ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

# “እንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ ቴአትር ባህሪያት አንፃር”

በ

ዮርዳኖስ ገረመው

የጥናቱ አማካሪ

ሽኩር ናስር

ነሃሴ 14/ 2013 ዓ.ም

# “እንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ ቴአትር ባህሪያት አንፃር”

በ

ዮርዳኖስ ገረመው

የጥናቱ አማካሪ

መ/ር ሽኩር ናስር

ለአርትስ ኦፍ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ነሃሴ 14/ 2013 ዓ.ም

## ምስጋና

በቅድሚያ ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ሰርቼ እንዳጠናቅቅ ለረዳኝ የአለም ፈጣሪ ለሆነው ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ለተወለደው ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው። ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ እንድሰራ ምክር በመስጠት፣ስህተቴን በማረም ለዚህ እንድበቃ ላደረገኝ ለአማካሪዬ ለመምህር ሽኩር ናስር ምስጋናዬ ከልብ ነው። በሃሳብ ለረዳችሁኝ ጓደኞቼ ልባዊ ምስጋናዬ ባላችሁበት ይድረሳችሁ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ እንግዳ ተውኔትን ከአብዘርድ የቴአትር መለያ ባሪያት አንፃር የሚያቀርብ ነው፡፡ አጥኚው እንግዳ ተውኔትን ከአብዘርድ የቴአትር መለያ ባሪያት እና ከአብዘርድ የቴአትር አላባውዊያን አንጻር ተንትኗል፡፡ አጥኚው የተነሳበትን የትናቱን አላማ ለማሳካት የተጠቀመው የጥናት አይነት ገላጭ የምርምር አይነት ሲሆን መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመባቸው እንግዳ ተውኔትን ደጋግሞ በማንበብ እና አጥኚው ለጥናቱ የሚጠቅሙትን የሀገር ውስጥ እና የውጪ ሀገር መፅሀፍትን በማገላበጥ ነው፡፡ በተገኘው የጹሁፍ ማስረጃ መሰረት እንግዳ ተውኔት የአብዘርድን አላባውያን ማሟላቱን የፈተሸበት ነው፡፡

# ማውጫ

ምስጋና ........................................ I
አጠቃሎ ........................................ II
ምዕራፍ አንድ........................................ 1
1. መግቢያ ........................................ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ........................................ 2
1.2. የጥናቱ አላማ........................................ 2
1.2.1 ዓብይ አላማ........................................ 2
1.2.2 ንዑስ አላማ........................................ 2
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ........................................ 3
1.6. የጥናቱ ዘዴ........................................ 3
1.6.1. የጥናቱ አይነት........................................ 3
1.6.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........................................ 4
1.7. የጥናቱ አወቃቀር ........................................ 4
ምዕራፍ ሁለት........................................ 6
2. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት........................................ 6
2.1. አብዘርድ እንደ ፍልስፍና........................................ 6
2.2. የአብዘርድ ቴአትር አመጣጥ ........................................ 7
2.3. የአብዘርድ ተውኔት መለያ ባህሪያት........................................ 8
2.4. "አብዘርድ ተውኔት" ከተውኔት አላባውያን አንፃር ........................................ 9
2.4.1. ገፀ ባሕርያት ........................................ 9
2.4.2. ቃለ ተውኔት........................................ 10
2.4.3. ሴራ ........................................ 12
2.4.4. መቼት ........................................ 13
2.4.5. ጭብጥ ........................................ 13
ምዕራፍ ሶስት........................................ 15
3. የመረጃ ትንተና ........................................ 15
3.1. የእንግዳ ተውኔት አፅመ ታሪክ........................................ 15
3.2 የእንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ ተውኔት አላባውያን አንጻር ........................................ 17
3.2.1 "የእንግዳ" ተውኔት የገፀባህሪያት አሳሳል ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላሉ?........................................ 17
3.2.2 "የእንግዳ" ተውኔት መቼት ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላሉ? ........................................ 27

3.2.3 “የእንግዳ” ተውኔት ቃለተውኔት ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላል? ..................................28
3.2.4 “የእንግዳ” ተውኔት ሴራ ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላል? ...........................................33
3.2.5 “የእንግዳ” ተውኔት ጭብጥ ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላል?........................................34
3.3 እንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ ተውኔት መለያ ባህሪያት አንጻር ......................................................................37
ምዕራፍ አራት ........................................................................................................................................ 40
4. ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ ................................................................................................................. 40
4.1. ማጠቃለያ ........................................................................................................................................ 40
4.2. የመፍትሔ ሀሳብ .................................................................................................................................41
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው
ዋቢ መጽሃፍት

**የአማካሪው ማረጋገጫ**

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማማከሪያ መስፈርት መሰረት የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለው፡፡

**የአማካሪው ስም**

**ፊርማ**

ይህ በተማሪ ዮርዳኖስ ገረመው "እንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ መለያ ባህሪያት አንጻር የተሰራ የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ጽሁፍ የዩንቨርሲቲውን ጥናት ደርጃ ያሟላ እና የቴአትር ጥበባት ት/ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑ ማረጋገጫ ነው፡፡

**አማካሪ ሽኩር ናስር**

**ፊርማ**

**ፈታኝ1**

**ፊርማ**

**ፈታኝ2**

**ፊርማ**

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ተውኔት ከኪነ ጥበብ ዘርፍ አንዱ ሲሆን እንዲሁም በተመሳሳይ በስነፅሁፍ ዘርፍ ይመደባል። ተውኔት ከፅሁፍ ረቂቅነት አልፎ ለመድረክ ዝግጅት ሲበቃ ከኪነ ጥበብ ዘርፍ ይመደባል። ፅህፈተ ተውኔት ለመድረክ ከመብቃቱ በፊት በፅሁፍ ደረጃ ያለ ለህትመት የበቃ አልያም ለህትመት ያልበቃም ሲሆን በስነ ፅሁፍ ዘርፍ ውስጥ ይካተታል። ፋንታሁን እንግዳ *"የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ" (2009፤9)* በሚለው መፅሀፍ ውስጥ ስለተውኔት አራት ፍቺዎችን ያስቀምጣል። *"ሙሉ የተውኔት ድርሰት፤የተውኔት ትምህርት መስክ፤ ከተውኔት ድርሰት አንዱ ክፍል ወይም ትዕይንት፤መድረክ ላይ ያለ የተውኔት ዝግጅት ትርጉሞችን ያካትታል። "*

አጥኚው ፋንታሁን እንግዳ ከሰጣቸው አራት የተውኔት ፍቺዎች መካከል "ሙሉ የተውኔት ድርሰትን" የሚያጠና ይሆናል። የተውኔት ድርሰት ከእለት እለት ኑሮአችን የሚቀዳ ምናባዊ ፈጠራ ነው። አጥኚው "እንግዳ" ተውኔትን ከአብዘርድ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ስልት እና ከአብዘርድ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር" በዚህ ጥናት ውስጥ ይተነተናል።

አብዘርድ ማለት ትርጉም የለሽ ወይም ኢ-አመክንዮአዊ ማለት ነው። ፋንታሁን እንግዳ *"የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ" (2009፤131)* በሚለው መፅሐፍ ውስጥ *"አብዘርድ ማለት ትርጉም የለሽ ወይም ኢ-አመክንዮአዊ ማለት ሲሆን የሰውን ልጅ የተስፋቢስነት ሁኔታ ኢዘልማዳዊ እና ኢ-አመክንዮአዊ በሆነ መንገድ የሚያሳይ የተውኔት አይነት ነው።"* አብዘርድ ከአንደኛው የአለም ጦርነት በኃላ የተነሳ ፍልስፍናዊ እንቅስቃሴ ሲሆን ለስነፅሁፍ ግብአትነት የተፈጠረ ሳይሆን እራሱን ችሎ የተለያዩ ጥያቄዎችን እና ሀሳቦችን የሚያነሳ እና የሚጥል ፅንሰ ሀሳብ ነው።

አጥኚው እንግዳ የተሰኘውን ተውኔት ከአብዘርድ የተውኔት መለያ ባህሪያት እና ከአብዘርድ የተውኔት አላባውያን ተንትኗል። እንግዳ የማንያዘዋል እንዳሻው ስራ ሲሆን ለምጀመሪያ ጊዜ በ1985 ለመድረክ የበቃ ሲሆን በ2000 አመተ ምህረት በድጋሚ ተጽፎ ለመድረክ በተደጋጋሚ ለመድረክ ቀርቧል።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቴአትር ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን ተፅፎ ከታየበት ጊዜ አንስቶ እስከአሁን ዘመን ድረስ የተለያዩ ዘውግ ያላቸው ቴአትሮች በሀገራችን ፀሀፊ ተውኔቶች ተፅፈው ለእይታ የበቁ ሲሆን ከነዚህ የተለያዩ ዘውግ አካላቸው የሀገራችን ቴአትሮች ውስጥ በአብዘርድ ፅንሰ ሀሳብ ላይ ተመርኩዘው ተፅፈው ለመድረክ የበቁ ጥቂቶች ናቸው። “Six plays, from west & east Africa” በሚለው የተውኔቶች ስብስብ መጽሃፍ ውስጥ የማንያዘዋል እንዳሻው “እንግዳ” የተሰኘው ተውኔት ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉሞ በእንግሊዝ ሃገር ውስጥ የታተመ ሲሆን በትንሹም ቢሆን በሃገራችን ቴአትር ያለበትን ሁኔታ ለአለም አስተዋውቋል። አጥኚው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ያነሳሳው ምክንያት እንግዳ የተሰኘውን ተውኔት ከሃገር ውስጥ አልፎ ለአለም የበቃውን ተውኔት በሃገር ውስጥ የተውኔት አፍቃሪያን ለማስተዋወቅ እና እንግዳ የተሰኘው ተውኔት እንግሊዝ ሃገር ተተርጉሞ በታተመበት ወቅት ተውኔቱ የአብዘርድን የተውኔት አጻጻፍ ያሟላል ተብሎ ሲሆን አጥኚው ይህን ተውኔት የአብዘርድ ቴአትር አላባውያንን፣የአብዘርድ ቴአትር መለያ ባህሪያትን ያሟላል? ወይም አያሟላም? የሚለውን ለመገምገም እና ለመተንተን ነው።

## 1.2. የጥናቱ አላማ

### 1.2.1 ዓብይ አላማ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ "እንግዳ"ተውኔትን ከአብዘርድ ቴአትር ባህሪያት አንፃር መተንተን እና ማብራራት ነው።

### 1.2.2 ንዑስ አላማ

- የእንግዳ ተውኔትን ጠንካራ እና ደካማ ጎን መተንተን
- እንግዳ ተውኔትን ከአብዘርድ ተውኔት የገጸባህሪያት አሳሳል አንጻር መተንተን
- እንግዳ ተውኔትን ከአብዘርድ ተውኔት የሴራ አወቃቀር አንጻር መተንተን
- እንግዳ ተውኔትን ከአብዘርድ ተውኔት የጭብጥ አገላለጽ አንጻር መተንተን
- እንግዳ ተውኔትን ከአብዘርድ የመቼት አገላለጽ አንጻር መተንተን
- እንግዳ ተውኔትን ከአብዘርድ ተውኔት የቃለተውኔት አገላለጽ አንጻር መተንተን

## 1.3 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- “እንግዳ” ተውኔት የአብዘርድ ቴአትርን መለያ ባህሪያት ያሟላል?
- እንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ የተውኔት ገጸባህሪያት አሳሳል አንጻር ምን ይመስላል?
- እንግዳ ተውኔት የአብዘርድን የተውኔት ሴራ አወቃቀር ያሟላል?
- እንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ የተውኔት ጭብጥ አገላለጽ አንጻር ያሟላል?
- እንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ የተውኔት መቼት አገላለጽ አንጻር ያሟላል?

## 1.4. **የጥናቱ ጠቀሜታ**

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ሲኖሩት ከነዚህም መካከል ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ የሚመለከት ማንኛውም ሰው ስለአብዘርድ ፍልስፍናዊ ፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ይኖረዋል። የአብዘርድን ፅንሰ ሀሳብ ተመርኩዞው አንድ ተውኔት ለሚፅፉ ፀሀፈ ተውኔቶች እንዴት መፃፍ እንዳለባቸው ፍንጭ የሚሰጥ ይሆናል።ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ተመልክተው "እንግዳ"ተውኔትን ለሚያነቡ፣ለመድረክ ማብቃት ለሚፈልጉ፣ አልያም በድጋሚ ለመድረክ የሚበቃ ከሆነ ስለ "እንግዳ"ተውኔት ዘውግ፣ቅርፅ፣ጭብጥ የተሻለ እና ግልፅ የሆነ ማብራሪያ ለመስጠት ይሞክራል። ከዚህ በኋላ በአብዘርድ የተውኔት አጻጻፍ ላይ ተመርኩዘው ለሚጻፉ ደካማ ጎኑን በመተው ጠንካራ ጎኑን በመውሰድ ትምህርት የሚያገኙበት ይሆናል። በስተመጨረሻም በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ ተመርኩዘው ጥናት ለሚሰሩ እንደ ተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝትነት ያገለግላል።

## **1.5 የጥናቱ ወሰን**

የዚህ ጥናት ወሰን "እንግዳ"ተውኔትን ከአብዘርድ ተውኔት መለያ ባህሪያት እና ከተውኔት አላባውያን አንፃር መገምገም ነው።

## 1.6. **የጥናቱ ዘዴ**

### *1.6.1. የጥናቱ አይነት*

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ የምርምር አይነት ተከትሎ የተሰራ ነው። ያለው እንዳውቅ "የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር"(2009፣21) በሚለው መፅሐፍ ውስጥ ስለገላጭ ምርመር እንዲህ ሲል ያትታል "ገላጭ ምርምር ስሙ እንደሚያመለክተው ተመራማሪው አንድ ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምንያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚያቀርቡበት ነው።"አጥኚው

ይህን ገላጭ የጥናት አይነት በመጠቀም "እንግዳ" ተውኔትን ከአብዘርድ ቴአትር መለያ ባህሪያት እሳቤ እያነጻጸረ አሟልቷል ወይም አላሟላም የሚለውን ተንትኗል።

### 1.6.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ የጥናቱ አይነት እና ጥናቱን የሚሰበስብበት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ይኖሩታል። አጥኚው "እንግዳ" ተውኔትን ከአብዘርድ ቴአትር መለያ ባህሪያት አንፃር ለመስራት የሚጠቀምባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መዛግብትን(documents)ነው።

#### 1.6.2.1. መዛግብት (documents)

መዛግብት በፅሁፍ ደረጃ ያሉ ለህትመት የበቁ ወይም ለህትመት ያልበቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ያለው እንዳወቅ ሙሉ(ፕሮፌሰር) "የምርምር መሠረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር"(2009፣191) በሚለው መፅሀፉ ውስጥ ስለመዛግብት እንዲህ ሲል ያብራራል"መዛግብት ተመራማሪው ስላለፈም ይሁን ወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲነሳ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው።መዛግብት በፅሁፍ መልክ ከየቤተ መፅሀፍቱ፣ከየቤቱ መዛግብቱ ወይም ከሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎች እና እንደ ሁኔታውም ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው።"

አጥኚው ይህን ጥናት ለማድረግ የተለያዩ መዛግብቶችን አገላብጧል። እንደ መፅሃፍት፣ጋዜጦች፣ መፅሔቶችን፣ጥናታዊ ፅሁፎችን፣ድህረ ገፆችን ተጠቅሟል።

## 1.7. የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አላማ፣ጥናቱ የሚዳስሳቸው ጥያቄዎች፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ ወሰን፣የጥናቱ ዘዴ፣የጥናቱ አወቃቀር እና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ይዳስሳል።በምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ላይ ተመርኩዞ አብዘርድ እንደ ፍልስፍና፣የአብዘርድ ቴአትር አመጣጥ፣የአብዘርድ ቴአትር መለያ ባህሪያት እና አብዘርድ ተውኔት ከተውኔት አላባውያን አንጻር በሚሉት ንኡሳን ርእሶች ትንተና ሰጧል።

በምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ዋነኛ ክፍል ሲሆን አጥኚው በምዕራፍ ሁለት ያስቀመጣቸውን ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ተጠቅሞ የአጥኚው የራሱን ሀሳብ ጨምሮ ሰፊ ማብራሪያ እና ትንተና የሚሰጥበት ነው። የማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳቦች በምዕራፍ አራት የሚሰጡ ናቸው።

## 1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኚው ይህን ጥናት በሚያደርጉበት ወቅት የገጠመው የዋነኛው ችግር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናታዊ ጽሁፎችን ማግኘት አለመቻሉ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት

### 2.1. አብዘርድ እንደ ፍልስፍና

እንደ ማርቲን ኢስሊን ገለፃ *"The Theatre of The Absurd"(1961፤19)* አብዘርድ ማለት "በሙዚቃዊ እሳቤ ከህብረ ዘማሪዎች ማፈንገጥ ወይም ህብረ ዘማርያን በአንድ አይነት የዜማ ቅኝት ውስጥ ሁነው እየዘመሩ ከመካከላቸው ያለ አንድ ግለሰብ የሚዘምርበት የዜማ ቅኝት ከሌሎቹ ሲለይ ማለት ነው። በመዝገበ ቃላት ፍቺ ላይ ከህብረ ዘማርያን ማፈንገጥ ማለት ከምክንያታዊነት ጋር የማይጥም፣የማይመች በአጠቃላይ አብዘርድ ማለት አስቂኝ ማለት ነው።"[1] ጃሬድ ስሚዝ *"From One to All the Evolution of Camus's Absurdism" (2020፤7)* በሚለው ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ደግሞ አብዘርድ ማለት "በሰው እና በህይወቱ(በነፍሱ) በተዋናይ እና መቼት መካከል ፍቺ ሲኖር ማለት ነው።"[2]

የአብዘርድ ፍልስፍና የሚያመለክተን የሰው ልጅን በዚህ ዓለም የመገኘቱን ትርጉም መሻት እና አንዳችም አለማግኘቱን ነው። ይህን ሀሳብ ጄሬድ ስሚዝ (2020፤8) በዚሁ ጥናታዊ ፅሁፉ ላይ እንዲህ ሲል ይደግፈዋል "አብዘርድ የተፈጠረው የሰው ልጅ ፍላጎት መናር እና ምክንያታዊ ባልሆነችው ዓለም መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ነው።"[3] *"The Theatre of The Absurd"* በሚለው መፅሀፉ ላይ ማርቲን ኢስሊን ደግሞ (1961፤19) "አብዘርድ ማለት አላማ የሌለው ባዶ ማለት ነው። የሰውን ልጅ ስር ከሰደደው ሀይማኖታዊ ድርጊቱ ማቆራረጥ እና ድርጊቶች ትርጉም የለሽ እና የማይረቡ እንደሆኑ ማድረግ ነው የአብዘርድ አላማ።"[4] "የአብዘርድ ፍልስፍና የሚያጠናው በሰው ልጆች የመኖር ዝንባሌ ውስጥ የሀይማኖትን ትርጉም መሻት እና ተፈጥሯዊ እሴትን የማግኘት መሠረታዊ ጥያቄ ሲኖር ነገር ግን ይህቺ ዓለም ምክንያት አልባ መሆኗ እና አላማ የሌላት መሆኗ ነው።"[5]

**Ansel Pereira (2019)**

## 2.2. የአብዘርድ ቴአትር አመጣጥ

የአብዘርድ ተውኔት የተነሳው ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በኃላ ነው። ይህን ሀሳብ ፋንታሁን እንግዳ *"ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ሀ አስከ ፐ" (1993፣78)* በሚለው መፅሀፉ ላይ እንዲህ ሲል ያጠናክረዋል፡-

> “ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኃላ በአውሮፓ እና አሜሪካ የተከሰተ ትኩስ ተውኔታዊ ዘውግ ነው።ይህን የተውኔት ዘውግ የፈጠረው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ሰፍኖ የነበረው ተስፋ አስቆራጭ ማህበራዊ እውነታ ነበር። በጦርነቱ የጅምላ ፍጅቶች፣የህይወት እና የንብረት ውድመት የህዘብ መፈናቀል እና ስደት፣የፍትህ እጦት የአስተዳደር መፋለስ በመስፈኑ ፀሀፊ ተውኔቶች ይህን ተስፋቢስ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እንዳለ ለማሳየት ሲሉ የአጎለበቱት አዲስ የተውኔት ዘውግ ነው።"

አብዘርድ የሚለውን ስያሜ ለመጀመሪያ የተጠቀመው ማርቲን ኢስሊን እንደሆነ ይታመናል። *"የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ"* በሚለው መፅሀፉ ውስጥ ፋንታሁን እንግዳ (2009፣131) ይህን ሀሳብ እንዲህ ሲል ያጠናክረዋል "አብዘርድ የተውኔት አይነት ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረው እና ጥቅም ላይ የዋለው በማርቲን ኢስሊን ነው።"

እንደ በሮኬት እና ሌሎች ገለጻ *“History of the Theatre”(2008፣454)” “የአብዘርድ ቴአትር መጻፍ የጀመረው በ1939 ሲሆን ለእውቅና የበቃው ግን በ1950ዎቹ ውስጥ ነው።”[6] በዚሁ በሮኬት እና ሌሎች መጽሃፋቸው ላይ ወረድ ብሎ።(2008፣456) “የአብዘርድ ቴአትር ዘልማዳዊ የቴአትር መዋቅር የለውም። ማለትም መጀመሪያ፣መሃል እና መጨረሻ ካለው የሴራ መዋቅር ጋር ግንኙነት የላቸውም። በዚህ የቴአትር አጻጻፍ ላይ የሚታወቁት ሳሙኤል ቤኬት እና ዩጂን ኢዩኒስኮ ናቸው። የሳሙኢል በኬት ስራዎች በስነመለኮታዊ ላይ ሲያተኩሩ የዩጂን እዩኔስኮ ስራ ደግሞ በማህበራዊ ግኝኙነት ላይ ያተኩራል።”[7]*

## 2.3. **የአብዘርድ ተውኔት መለያ ባህሪያት**

ባህሪ ማለት የአንድ ነገር መገለጫ ወይም መለያ ማለት ነው። የአብዘርድ ተውኔትም እንደሌሎቹ የተውኔት ኢዝሞች፣ዘውጎች እና ቅርጾች የራሱ የሆኑ መለያ ባህሪያት አሉት። እንደ ሶማንታህ ሳርከር ገለጻ ወደ ሰባት የሚጠጉ የአብዘርድ መለያ ባህሪያትን አስቀምጧል። እንደሚከተለው በዝርዝር ተቀምጠዋል።

*1. የመኖር ጥያቄ*

*"የአብዘርድ ተውኔቶች መሠረታዊ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ። ለምድነው በህይወት የምንኖረው? ለምንድንስ ነው የምንሞተው? ለምንስ ግፍ እና ስቃይ ይደርስብናል።"[8]*

***2. ትርጉም አልባ ቃለ ተውኔት***

*"በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ቋንቋ ትርጉም አልባ ነው። ምክንያቱም ቋንቋቸው የሰውን ልጅ የመኖር ህልውናዊነት ስለማይገልፅ።"[9]*

***3. ምክንያት አልባ ንግግሮች እና ትርጉም አልባ ሴራዎች***

*"በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ምክንያት አልባ ንግግሮች እና ትርጉም የለሽ ሴራዎች የራሳቸውን ነፃ ዓለም መገንባት ይፈልጋሉ።"[10]*

***4. የሰው ልጅ ከዓለም ጋር በድጋሚ እንዲስማማ ማድረግ***

*"ተረት እና የአለም ስርአቶችን በሰው ልጅ ህይወት ወስጥ ያለውን ጠቀሜታ መመለስ እና የህይወትን የመጨረሻ እውነታዎች እንዲረዱ ማድረግ።"[11]*

***5. ረቂቅ የህይወት እሴቶች ላይ አፅንኦት መስጠት***

*"የአብዘርድ ተውኔቶች ግፊት ያደርጋሉ እንደ ፍቅርና እና ቤተሰብ ያሉ ረቂቅ ጉዳዮችን እንድንመለከት ያስገድደናል። ስለዚህ የህይወትን ትርጉም የለሽነት አምነን እንድንኖር ያደርጋል።"[12]*

የአብዘርድ ትውኔቶች የአለምን ትርጉም አልባነት፣የአለምን ጨለማነት የሚያሳዩ ሲሆን በዚህ ሂደት ውስጥ ግን ብርሃንን ሲፈልጉ ይስተዋላል። በአብዘርዳዊ ሂይወት ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ከሚውስዷቸው የምፍትሄ ሃስቦች መካከል አንደኛው የሂይወትን አብዘርድነት አምነንን መቀበል ነው። የሂይወትን አብዘርደነት አምነን ስንቀበል ደግሞ በድጋሚ ወደዚህ አብዘርዳዊ ህይወት እንዳንመለስ ፍቅር እና ቤተሰብ አንደኛው መፍትሄ ነው።

*6. ግልጽ ያልሆኑ ቦታ፣ጊዜ እና ገፀባህሪዎች*

*"አብዘርዲስቶች ያለፈ ወይም የወደፊት የሚባል ነገር የላቸውም የአሁንም ቢሆን ድግምግሞሽ ነው አዲስ ነገር የለም ብለው ስለሚያምኑ በተውኔቶቻቸው ውስጥ ጊዜ እና ቦታው የት እንደሆነ አይታወቅም ገፀባህሪዎች ማን እንደሆኑ አይታወቅም።"[13]*

*7. በገፀባሪዎች መካከል የግንኙነት አለመኖር*

*"እያንዳንዱ ገፀባህርይ የራሱን ግላዊ ኑሮው የሚኖር ሲሆን እሱን እንዲረዳው ሌላ ገፀባህርይ ለማግኘት ይሞክራል እናም ይህ ሙከራ የበለጠ በሁለቱ በገፀባሪዎች መካከል እርቀትን ይፈጥራል።"[14]*

Somnath Sarkar, (may 28,2021)

## 2.4. "አብዘርድ ተውኔት" ከተውኔት አላባውያን አንፃር

የተውኔት አላባውያን አንድን ተውኔት የተሟላ እና እራሱን ችሎ እንዲቆም የሚያስችሉ ግብአቶች ናቸዉ። ይህን ሀሳብ የሚያጠናክርልን የሻው ተሰማ *"የተውኔት አፃፃፍ መነፀር" (1998፤41)* በሚለው መፅሀፋ አላባውያንን እንዲህ ሲል ይገልፀዋል "አላባውያን ማለት ከስነፁሁፋዊ አተያይ አኳያ አንድን የፈጠራ ስራ በማዋቀር ሂደት የተሟላ ዘውግ አድርጎ ለማቅረብ የሚያስችሉ ተካታች ቁምነገሮች እንደ ማለት ነው። ከተውኔት አንፃር አላባውያን ስንል ተውኔቱን ምልአተ እንዲኖረው የሚያበቁ የመገንቢያው ውህዳን እና የተዝናኖቱ መስፈርት ናቸው ማለት ይቻላል።"

የአንድ ተውኔት አላባውያን የምንላቸው ገፀባሕርያት፣መቼት፣ቃለ ተውኔት፣ሴራ እና ጭብጥ ናቸው። አጥኚው አንድ የአብዘርድ ተውኔት ከነዚህ የተውኔት አላባውያን አንፃር ምን ሊመስል ይችላል የሚለውን የሚፈትሽ ነው።

### 2.4.1. ገፀ ባሕርያት

ገፀ ባሕርያት ሙሉ ለሙሉ በደራሲው የተፈጠሩ አልያም ደግሞ በገሀዱ ዓለም የሚገኙ እውነተኛ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ጫንያለው ወ/ጊዮርጊስ እና ሌሎቹ "*መሠረታዊ የተውኔት አፃፃፍ መርሖዎች*" (200፤ 42) በሚለው መፅሃፋቸው እንዲህ ሲሉ ይህን ሀሳብ ያጠናክሩታል "ገፀባሪያት ተውኔቱን ለማራመድ በፀሀፊው የተፈጠሩ እና በድርሰቱ ውስጥ የሚኖሩ የድርጊት ወኪሎች ናቸው። እያንዳንዱ ገፀባህሪ ከሌላው

ገፀባህሪ በግልጽ የተለየ ማንነት ሊኖረው ይገባል። በእድሜ፣በአቋም/በተክለ ሰውነት/፣በእምነት፣በአስተዳደግ ወይም በአነጋገር/ቋንቋ/ ወዘተ ልንለያቸው ይገባል።"

የአብዘርድ ገፀባሕርያት አሳሳል ከላይ እንዳየነው ዘልማዳዊ ከምንለው የገፀባህሪያት አሳሳል የሚመደቡ አይደለም። ማርቲን ኢስሊን *"The Theatre of The Absurd"(1961፤300)* በሚለው መፅሀፉ ውስጥ እንዲህ ሲል የአብዘርድ ገፀባሕርያትን ምንነት ያስረዳል "በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ገፀ ባሪዎችን ምን እንዳነሳሳቸው እና ምን እንደሚያደርጉ ለመገመት እጅግ አዳጋች ነው። በድርጊታቸው እና በተፈጥሮአቸው ይታይባቸዋል። የዓለምን አስከፊነት እንድንመለከት የሚያደርጉን በገፀባህሪው መሪነት ነው።"[15] *"የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ"* በሚለው መፅሀፉ ፋንታሁን እንግዳ (2009፤132) የአብዘርድ ገፀ ባሕርያት ምንነት ያስረዳል "በአብዘርድ ተውኔት ተስፋቢስ ገፀባሕርያት የሚከሰቱት በልዩ ልዩ ቅርፅ እና ማንነት ነው። በአስፈለገበት ቦታ ሁሉ ፆታቸውን፣እድሜያቸውን እና በአጠቃላይ ስብዕናቸውን ቀይረው መቅረባቸው የተለመደ ነው"

በአብዘርድ ቴአትር ውስጥ ዕድሜያቸው፣ባህሪያቸው፣ስማቸው፣አመለካከታቸው፣አለባበሳቸው በትክክል ምን እደሆነ የማናውቅበት ጊዜ አለ። ፋንታሁን እንግዳ *"ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ሀ እስከ ፐ" (1993፤78)* በሚለው ሌላኛው መፅሀፉ ከላይ ያለውን ሀሳብ እንዲህ ሲል ያጠናክረዋል "የሚሳሉት ገፀባሕርያት የግል ታሪክም ሆነ ሰበበ ድርጊት የላቸውም። ይህ ማለት እንደ ትውፊታዊ የተውኔት ድርሰት ስለገፀባህሪያት ዳራዊ ታሪክ፣ስለቤተሰባቸው፣ስለሙያቸው፣ስለትምህርታቸው ትውውቅ አይደረግም ማለት ነው። በተውኔቱ ድርጊት የሚሳተፉ ገፀባህርያት ድርጊቱ በሚከናወንበት በቦታና ጊዜ ለመገናኘት ያበቃቸው ምክንያት ሳይገለፅ ዝም ብለው ይገናኙ እና ተውኔታዊ ድርጊቱን ይከውናሉ።"

እንደ ማርቲን ኢስሊን ገለጻ “theatre of the absurd” (1961፤402) “ገጸባህሪዎቹ እጅግ ውስብስቦች ናቸው። ምክያቱም በዙሪያቸው ያለቺው አለም ለመረዳት አዳጋች ስለሆነች ነው።”16

## 2.4.2. **ቃለ ተውኔት**

ቃለ ተውኔት ለአንድ የተውኔት ፅሁፍ ስራ ወሳኝ ተብለው ሊዘረዘሩ ከሚችሉ ነጥቦች ውስጥ አንደኛው እና ዋነኛው ነዉ። ደበበ ሰይፉ *"የቲያትር ጥበብ ከፀሀፊ ተውኔቱ አንፃር"(1973፤40)* በሚለው መፅሀፉ መቼት ማለት "ቁጥብነት ያለው ሴራውን ወደፊት እሚያራምድ መሆን አለበት።" ይህን ሀሳብ የሚያጠናክርልን ፋንታሁን እንግዳ *"ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ሀ እስከ ፐ" (1993፤43)*

"ቃለተውኔት ቢያንስ ሶስት ተጨባጭ ጠቀሜታዎች አሉት።እነዚህም አንደኛ የተውኔት አላባውያንን ያስተዋውቃል። ሁለተኛ ሴራውን ወደፊት ያራምዳል። ሶስተኛ የእያንዳንዱን ገፀባህሪ ምንነት ቁልጭ ባለ መንገድ ያስተዋውቃሉ።"

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ያሉ ገፀባሕርያት የሚናገሩት ለተመልካች ግራ የሚያጋቡ ናቸው። ወጥ እና ተመሳሳይነት ላይኖረው ይችላል። ማርቲን ኢስሊን *"The Theatre of The absurd"(1961፤21)* በሚለው መፅሀፉ ውስጥ የአብዘርድን ቃለተውኔት እንዲህ ሲል ያብራራዋል "ቋንቋ እጅግ ጠቃሚ ከሆኑት አላባውያን አንዱ ሲሆን በአብዘርድ ፅንሰ ሀሳብ ውስጥ ግን ገፀባሪዎች የሚናገሩት እርስ በርሱ የሚቃረን ነው።"[17]"ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ሀ እስከ ፐ" በሚለው መፅሀፉ እንደ ፋንታሁን እንግዳ ገላፃ(1993፤78)፦

> "ገፀባሕርያት እርስ በርስ የሚለዋወጡት ንግግር በአንዱ ቅንጣት ታሪክ ያለው ንግግራቸው በቀጣዩ ቅንጣት ታሪክ ከሚገኘው ንግግራቸው ጋር የጠበቀ ግንኙነት የለውም። ገፀባህርያት በሚናገሯቸው ቃለተውኔቶች ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተ ነገሮች ሰዋሰዋዊ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ አይደሉም። የሚነገሩ ቃላት ትርጉም እንዲሁ የሚጠበቀውን የትርጉም አይነት የተሸከሙ አይደሉም። ገፀባሕርያት ሀይማኖትን፣ህግን፣ታሪክን እና ሌላም ርዕሰ ጉዳይን መሠረት በማድረግ ንግግር ቢለዋወጡ በንግግራቸው የሚጠቀሙበት ቋንቋ አንድነት ያለው አይደለም።"

የአብዘርድ ቋንቋ የሚከተለው ደንብ እና ስርአት ስለሌለው ቀጣዩ ላይ ምን ይላል ብሎ መገመት እና መተንበይ አይቻልም። ምክንያቱም ቋንቋው ያልተለመደ ለመገመትም አዳጋች ስለሆነ ነው።

አለን ሊውስ "The Theatre of the 'Absurd' – Beckett, Ionesco, Genet". The Contemporary Theatre: The Significant Playwrights of Our Time (1966፤260) በተሰኘው መጽሃፉ ደግሞ" "የአብዘርድ ቋንቋ በተውኔቶች ውስጥ ድግምግሞሽ የበዛበት እና ትርጉም የለሽ ቢሆኑም ተፈጥሮአዊነታቸውን የጠበቁ ናቸው።"[18]

የህይወትን አሰልቺነት፣እኔ ማን ነኝ፣ለምንድንስ ነው የተፈጠርኩት፣ደስታ የሚባለው ነገርስ ምንድን ነው እነዚህን እና እነዚህ መሰል ሌሎች ጥያቄዎችን አብዘርድ የሚያንጸባርቃቸው ሃሳቦች ናቸው ነው። እነዚህ ጥያቄዎች ደግሞ ተፈጥሮአዊ የሆኑ የሰው ልጆች ሃሳቦች ናቸው።

### 2.4.3. ሴራ

ሴራ ከተውኔት አላባውያን መካከል አንዱ ሲሆን የታሪክ እና የግጭት ድምር ውጤት ነው። ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክርልን ፋንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ሀ እስከ ፐ" (1993፤39) በተሰኘው መፅሀፉ ላይ እንዲህ ይላል "ሴራ ገፀባሕርያትን እና ግጭትን በዋናነት ይይዛል። የተውኔትን ወይም የልብ ወለድን አጠቃላይ ሴራ መናገር ማለት ገፀባሕርያት እንዴት በመጀመሪያ ግጭት ጀምረው እንዴት እንደሚያከሩት፣ከዚያም እንዴት መፍትሔ እንደሚያስገኙለት መናገር ማለት ነው።"

ለስ ኤሲፍ "Empty figure on an empty stage: the theatre of Samuel Beckett and his generation"(2001፤1) *"ብዙ ጊዜ በአብዘርድ ተውኔቶች ላይ የሚስተዋሉ ሴራዎች ባዶነት፣ብቸኝነት፣ ምንምነት፣ሊፈቱ የማይችሉ የተወሳሰቡ ሚስጥሮች ማእከላዊ የአብዘርድ ሴራዎች ናቸው።"*[19]

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ በየትዕይንቶቹ መካከል የምክንያት እና የውጤት ግንኙነት የለም።ፋንታሁን እንግዳ *"ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ሀ እስከ ፐ"(1993፤78)* በሚለው መፅሀፉ ይህን ሀሳብ እንዲህ ሲል ያጠናክረዋል "አብዘርድ ተውኔት በአንጻሩ አመክኗዊነትን የጠበቀ የተውኔታዊ መዋቅር መርህን ይቃረናል። አጠቃላይ ተውኔቱ በቅንጣት ትዕይንቶች እና በቁርጥራጭ ታሪኮች የተሞላ ሲሆን እያንዳንዱ ቅንጣት ትዕይንት በምክንያት እና ውጤት የሚራመድ አይደለም።"

ብዙጊዜ በየተእይንቶቹ የምክንያት እና የውጤት ግንኙነት የለም። ወጥ የሆነ የሴራ መዋቅር የለውም። አንዳንድ ጊዜ ክብ በሆነ የሴራ መዋቅር ውስጥ ይዋልላል። አልፎ አልፎ በንግግሮች መሃል ምንም አይነት ሴራ አይኖርም።

የአብዘርድ ሴራ ድግምግሞሽ የሚበዛበት፣ለዛ የሌለው፣በየተይንቱ ወይም በየቃለትውኔቱ መሃል የሚቀያየር ነው። እንደ አለን አስትሮ ገለጻ *"Understanding Samuel Beckett"(1990፤116)* በሚለው መጽሃፍ ውስጥ "አብዛኞቹ የአብዘርድ ሴራዎች በሁለት እርስ በርስ በተጣመሩ ጥንዶች መካከል የሚካሄድ ነው። በተለምዶ በሁለት ወንዶች አልያም በወንድ እና በሴት መካከል ነው።"[20]

ይህ የሚሆንበት ምክንያት በነዚህ ሁለት ግለሰቦች መካከል የሚያስተሳስራቸው አንድ ላይ የሚያደርጋቸው አንድ የጋራ ሃሳብ ስላላቸው ነው። ይህም ሃሳብ ሁለቱም ገጸባህሪዎች አንድ ያደረጋቸው ለአለም ያላቸው አመለካከት ነው። ይህ አመለካከታቸው የህይወት አሰልቺነት፣ባዶነት፣የማንነት ጥያቄ ሊሆኑ ይችላሉ።

### 2.4.4. **መቼት**

መቼት ከተውኔት አላባውያን መካከል አንዱ ሲሆን ፋንታሁን እንግዳ *"ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ሀ እስከ ፐ" (1993፤25)* በሚለው መፅሀፉ ውስጥ "መቼት ሶስት አብይት ክፍሎችን የያዘ ከልብ ወለድ፣ከተውኔት፣ከተራኪ ግጥም አላባውያን አንዱ ነው። መቼትን መቼት የሚያሰኙት የድርጊቱ ጊዜ፣ የድርጊቱ ቦታ እና ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ያለው ማህበራዊ እውነታ ናቸው።"

የአብዘርድ መቼት የማይታወቅ ከመሆናቸው ባሻገር አንድ የተወሰነ የማይቀር ቦታ ላይ ሊያርፍ ይችላል። ፋንታሁን *እንግዳ "የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ" (2009፤132)* በሚለው መፅሐፍ ውስጥ "የገፀባህሪያት አሳሳል ኢመደበኛ እና ኢዘልማዳዊ እንደሆነ ሁሉ የአብዘርድ ተውኔት መቼትም ባብዛኛው ውስንነት የለውም። ተውኔታዊ ጊዜውም ቦታውም ማህበራዊ እውነታውም ላይታወቅ ይችላል። ለዚህ ምክንያቱ በሰው አካል እና በሰው አምሳል የሚቀረፀው ገፀባህሪ ትርጉመ ቢስ ከመባሉ የተነሳ የሚኖርበት ቦታ እና ጊዜም አብሮ ትርጉም የለሽ ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው።"

### 2.4.5. **ጭብጥ**

የሰው ልጅ ህልውና በሰቃይ፣ በጭካኔ እና በአደጋ የተሞላ ነው፡፡ ይህ አይነቱ ገጠመኝ ታዲያ አሁን ላለው ማህበረሰብ ህይወት ዋጋ ማጣት የጀርባ አጥንት ሆኖአል፡፡ ታዲያ ይህን እንደ እውነታ የተቀበሉ ሰዎች በወለፈንዲ አዘቀት ውስጥ የዘፈቃሉ፡፡ ከዚያም በሂደት ብቸኝነት፣ ፍራቻና ተስፋ መቁረጥ የዘመናቸው የእለት ተእለት ሸክም ይሆንባቸዋል፡፡ ብቸኝነት እና ግራ መጋባት ጭንቅላታቸውን ይሞላዋል፡፡ የአብዘርድ ቴአትር ይህንን የሰው ልጅ እውነታን በጭብጥ ያንፀባርቃል፡፡ እንደ ፋንታሁን እንግዳ ገለፃ *"ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ሀ እስከ ፐ" (1993፤112)* "ጭብጥ ማለት በስነፅሁፋዊ ስራዎች ማለትም በተውኔት፣በልቦለድና በግጥም ፈጠራዎች ውስጥ ማእከላዊ ወይም ገዢ የሚባለው ረቂቅ ሀሳብ ነው። የአብዘርድ ጭብጥ ብቸኝነትን እና የመነጠል እንዲሁም የህይወትን እና የሞትን እርባናቢስነትን ያሳያል። " እንደ ማርቲን ኢስሊን ገለፃ *"The Theatre of The Absurd" (1961፤9)* በሚለው መፅሀፉ የአብዘርድን

ጭብጥ እንዲህ ሲል ያብራራዋል “የአብዘርድ ተውኔት ጭብጥ እጅግ ተመሳሳይ፣አሰልቺ እና አላማ የሌለውን ህይወትን ማሳየት ነው። የሰዎችን ስሜት አልባነት ለማሳየት እና ምክንያታዊነትን ወደ ጎን በመተው በሚፈጠሩ ሀሳቦች የሰው ልጆች እንዲያስቡ መንገድ ይከፍታል።"[21]

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የመረጃ ትንተና

### 3.1. የእንግዳ ተውኔት አፅመ ታሪክ

ሁለት አሰልቺ ህይወት ያላቸው እና ደስታ የራቃቸው ባልና ሚስት ይህን አሰልቺ ህይወት ለመርሳት መላ ሲዘይዱ ቤታቸው ውስጥ እንግዳ ጋብዘው በተጋባዡ እንግዳ ላይ መዝናናት፣መደሰት እና ይህን አሰልቺ ህይወታቸውን ለመርሳት ያስባሉ።ይህን ሀሳባቸውን በተደጋጋሚ የተለያዩ እንግዶችን እየጋበዙ ይከውኑታል። ባል እና ሚስት እንግዳ ወደ ቤታቸው የሚጋብዙት በየተራ ሲሆን በዚህኛው ሳምንት እንግዳ ወደ ቤታቸው የመጋበዝ ተራ የሚስት ነበረ። ሚስት ወደ ቴአትር ቤት በማምራት ለባሏ እና ለራሷ ለሚስት ጨዋታ የሚስማማትን እንግዳ ተዋውቃ ወደ ቤቷ እንዲመጣ ትጋብዘዋለች። እንግዳ በቀጠሮው ሰአት ቤት ሲመጣ ሚስት እቃ ለመግዛት ወደ ውጪ ወጣ ስልነበር ባል እንግዳውን ተቀብሎ እያጫወተ ያስተናግደዋል።

ባል ለእንግዳው ተዋናይ እንደነበር እና ጭቅጭቅና ውሸት ስለሰለቸው ሙያውን እንደተወው እንግዳውም የስነልቦና ባለሙያ እንደሆነ እና ሙያውን በፍላጐት እንደመረጠው ለባል ይነግረዋል። ባል አሁን ባለው የትዳር ህይወቱ ደስተኛ እንዳልሆነ እና አሁን ያገባትን ሚስቱን ከማግባቱ በፊት እጮኛ እንደነበረችው እና እጮኛውን አሁን ባገባት ሚስቱ እንደቀየራት ለእንግዳው ያጫውተዋል። እንግዳውም ለምን እንደዚህ እንዳደረገ ባልን ሲጠይቀው አሁን ያገባት ሚስቱ እንደወደደችው እና እራሷን ልታጠፋ እንደሆነ የሚስት ጓደኞች ሲነግሩት በድብቅ ከእጮኛው ተለይቶ ያገኛት ጀመር። በዚህ መሀል ሚስት ፍቅሯ እየጨመረ ሂዶ ጭራሽ እራሷን ለማጥፋት ሙከራ አደረገች። በስተመጨረሻም ባል "ምንድነው የምትፈልጊው" ብሎ ጠይቆ "አንተን ማግባት" ስትለው የበፊት እጮኛውን በመተው አሁን ያለችውን ሚስቱን እንዳገባት ያጫውተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ባል ቴአትር መስራት እንደሚወድ ነገር ግን መድረክ ላይ ሲወጣ እንደሚፈራ ለእንግዳ እያጫወተው እያለ ሚስት ከሄደችበት ተመልሳ ባል ሚስት እና እንግዳ ካርታ ይጫወታሉ። ባል ሁለት ካርታዎችን አንዴ ደርቦ ሲስብ ሚስት ትመለከተዋለች እነዳጭበረበረ ተረድታ ብትጠይቀውም ባል ግን እንዳላጭበረበረ ቢነግራትም ባለማመኗ የባልን ካርታ ስትቆጥር ሙሉ እንደሆነ እና እንዳላጭበረበረ ሲገባት ታፍራለች። ባልም ተናዶ በጥፊ ሲመታት ሚስት ወደ ውስጥ ትገባለች። ባል በዚህ መሀል አንድ ሀሳብ ይመጣለት እና እንግዳን ቦታ እንዲለዋወጡ ይጠይቀዋል።ይህ ማለት ባል "የእንግዳውን" ቦታ ሲይዝ

እንግዳው ደግሞ የ"ባልን" ቦታ የሚይዝ ነው። ሁለቱ በዚህ ሂደት እየተጨዋወቱ እያለ ባል በድንገት እራሴን አመመኝ ብሎ ወደ ውጪ ይወጣል። ባል ወደ ውጪ እንደወጣ ሚስት ትገባና የባል ፀባይ ግራ እንደሚያጋባ እና ከዚህ በፊት እሷን እንዴት እዳገኛት ለእንግዳው የነገረው ሁሉ ውሸት እንደሆነ እና የአዕምሮ በሽተኛ ታማሚ እንደሆነ ትነግረዋለች። ትዳራቸውም የውሸት እንደሆነ እና አባቷ ሳትወለድ በፊት እንደሞተ እና እናቷ ባል እግብታ ታናሽ እህት እንደተወለደላት እና እናቷ ከታናሽ እህቷ ይልቅ እሷን ብዙ ስራዎችን እንደምታሰራት እና አንድ ቀን ታናሽ እህቷን በጥፊ መታቻት።እናቷም እሷን በዱላ እንደቀጠቀጠቻት እና ባል ሆስፒታል ተመላልሶ እንዳሳከማት እና እሱ ቤት እንድታርፍ ስላደረጋት ታሪክ ህይወት እንደመረራት ከባሏ ጋር መኖር እንደማትፈልግ እያሰቃያት እንደሆነ ለእንግዳው ትነግረዋለች። አብራው እንድትሄድ እና አብረው መኖር እንደሚችሉ እንግዳው ለሚስት ሀሳብ ያቀርብላት እና ሚስትም ተስማምታ ከእንግዳው ጋር ከቤት ሊወጡ ሲሉ ባል ከውጪ ይገባል።

ባልም ለእንግዳው ከስነልቦና ሙያ ይልቅ አንድ ታሪክ ነግሬህ ወደ ቴአትር ፅሁፍ ቀይረህ ለምን አይሳካልህም በማለት ለእንግዳው ሀሳብ ያቀርብለታል። ባልም ታሪኩን እንዲህ ሲል ለእንግዳው ያጫውተዋል። ሁለት ኑሮ ያሰለቻቸው ባል እና ሚስት ይሔን ጊዜ ለማሳለፍ ምን ቢያረጉ እንደሚሻል ሲወያዩ አንድ ሀሳብ መጣላቸው የውሸት ቲያትር ከመስራት እውነተኛ ቲያትር መስራት። በአንድ ምሽት አንድ እንግዳ ብቻ ታዲያ ጨዋታው እንዳይሰለች ሲሉ ሲጀመር ቲያትር መሆኑን አይነገሩትም። ምክንያቱም ከነገሩት ጨዋታው ስለሚበላሽ። ይህን ታሪክ ባል ለእንግዳው ሲነግረው እንግዳ የሰማው የባል እና የሚስት ታሪክ መሆኑ ሲገባው ደርቆ ይቀራል። በእንግድነት ቤታቸው ከመጣ ጀምሮ የተረኩለት የየግል ታሪካቸው የውሸት እንደሆነ ይነግሩታል። እንግዳውም በመናደድ ባል እና ሚስት ይህንን ጨዋታ የሚያደርጉት እርስ በርሳቸው ስለሚጠላሉ መሸሸጊያ ፍለጋ እንደሆነ እና ሚስትም እንግዳው የተናገረው እውነት እንደሆነ እና ጨዋታውም እንዳስጠላት ለባል ትነግረዋለች። ባልም ሌላ ጨዋታ መቀየር እንደሚችሉ ለሚስት ቢያስረዳትም ሚስት ግን አሻፈረኝ በማለት ከእንግዳው ጋር ለመሔድ ትስማማለች።የሚስትን ለመሔድ መወሰኗን የተመለከተው ባል ወደ ውስጥ ገብቶ እራሱን በሽጉጥ ያጠፋል። በዚህ ጊዜ ሚስት እና እንግዳ ደንግጠው እርስ በርስ ይተያያሉ ሚስትም ወደ ውስጥ ገብታ ሁኔታውን አጣርታ ለእንግዳ ባል እንደሞተ ትነግረዋለች። እንግዳ ነገሩን ለፖሊስ እንደማያሳውቅ እና አብራው ሔዳ መኖር እንደምትችል ሀሳብ ያቀርብላታል ሚስትም እንግዳ ያቀረበውን ሀሳብ ተቀብላ ከእንግዳው ጋር ለመሄድ ትስማማእና በኃላ ላይ ግን ሀሳቧን ቀይራ ከባሏ እሬሳ ጎን መሆን እንደምትፈልግ ትነግረዋለች። እንግዳውም ወደ አቤቱታ ለመሄድ ሲነሳ ባል በአንድ እጁ ሽጉጡን ይዞ ከውስጥ ይወጣል። በድጋሚ እንደዋሹት እና ጨዋታ እንደሆነ ሲገባው እንግዳው በመናደድ ከቤቱ ወጦ ይሄዳል።

ቀጣይ እንግዳ የመጋበዙ ተራ የባል እንደሆነ ከተስማሙ ከጥቂት ደቂቃ በኃላ ሚስት ከዚህ በኃላ እንግዳ እየጋበዙ የሚጫወቱት ጨዋታ እንደ ሰለቻት እና መቅረት እንዳለበት ለባል ታሳስበዋለች። ባልም በመስማማት እስከዛሬ ከተጫዎታቸው ጨዋታዎች ውጪ አዲስ ጨዋታ ያመጣል። ጨዋታውም ሽጉጡ ውስጥ አንድ ጥይት ከቶ እራሳቸው ላይ እንዲተኩሱ ማድረግ ነበር። መጀመሪያ ባል እራሱ ላይ ለመተኮስ ይሞክር እና ፈርቶ ይተወዋል ሚስት ከባል እጅ ሽጉጡን ተቀብላ ወደ ራሷ ትተኩሳለች። ሚስትም በመደንገጥ ደርቃ ትቀራለች። በስተመጨረሻ ሚስት ባልን ሌላ ጨዋታ ይፈልግ እንደሆነ ትጠይቀዋለች ባልም ምን ያህል እንደጎዳት ሲረዳ ይቅርታ ይጠይቃታል።

## 3.2 የእንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ ተውኔት አላባውያን አንጻር

### 3.2.1 "የእንግዳ" ተውኔት የገፀባህሪያት አሳሳል ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላሉ?

የአብዘርድ ገፀባሕርያት አሳሳል ዘልማዳዊ ከምንለው የገፀባህሪያት አሳሳል የሚመደቡ አይደሉም። አጥኚው በምዕራፍ ሁለት የአብዘርድ ገፀባሕርያትን አሳሳል ለመጥቀስ እንደሞከረው "የአብዘርድ ገፀባሕርያት የግል ታሪክም ሆነ ሰበበ ድርጊት የላቸውም። ይህ ማለት በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ስለገፀባህሪያት ዳራዊ ታሪክ፣ስለቤተሰባቸው፣ስለሙያቸው፣ስለትምህርታቸው፣ትውውቅ አይደረግም ማለት ነው። በተውኔቱ ድርጊት የሚሳተፉ ገፀባሕርያት ድርጊቱ በሚከናወንበት ቦታና ጊዜ ለመገናኘት ያበቃቸው ምክንያት ሳይገለፅ ዝም ብለው ይገናኙ እና ተውኔታዊ ድርጊቱን ይከውናሉ።" በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ተስፋ ቢስ ገፀባሕርያት በተለያየ መንገድ ነው የሚገልፁት።

"በእንግዳ" ተውኔት ውስጥ ባል፣ሚስት እና እንግዳ የተሰኙ ሶስት ገፀባሪዎች ሲኖሩ የነዚህ ሶስት ገፀባሪዎች ግንኙነት ባል እና ሚስት የትዳር አጋሮች ሲሆኑ እንግዳ ደግሞ አሰልቺ ህይወታቸውን ለመርሳት ብለው ባል እና ሚስት በፈጠሩት ጨዋታ ውስጥ ተጋባዥ የሆነ ሰው ነው።

**ባል**

አጥኚው የባልን አጠቃላይ የገፀባህሪ አሳሳል ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር እንደሚከተለው አቅርቧል።

በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ከሚገኙት ሶስት ገፀባህሪዎች መካከል ባል አንዱ ነው። አጥኚው ከላይ ለመግለጽ እንደሞከረው የአብዘርድ ገጸባህሪያት የግል ታሪክም ሆነ ሰበበ ድርጊት የላቸውም። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ግን የባል ይኋላ ታሪክ ከሞላ ጎደል ይትወቃል ፆታው ወንድ፣ሙያው የቀድሞ ተዋናይ የነበረ፣ባለትዳር የሆነ

እና ቤተሰቡ ውጪ የሚኖሩ ናቸው። ከዚህ ውጪ ስለትምህርት ደረጃው፣ስለህይማኖቱ፣ስለመልኩ፣ ስለአለባበሱ የሚታወቅበት መንገድ የለም። ይህ የባል ማንነትን ከአብዘርድ የገጸባህሪያት አሳሳል አንጻር አጥኚው ሲመለከተው የሚጣረስ ሁኖ አግኝቶታል። ምክንያቱም በአብዘርድ ተውኔቶች ውስጥ የገጸባህሪያት የኋላ ታሪካቸው አይቀመጥም ከየት ይምጡ፣ወዴት ይሂዱ፣ስላለፈ የቤተሰቦቻቸው ታሪክ፣እዴት ከሌሎች ሰዎች ጋር እደተገናኙ አይገለጽም። ይህ የሚደረግበት ምክንያት ደግሞ ያለፈ ታሪካቸው አሁን ላይ ላለው አብዘርዳዊ ሂይወት ምንም ጥቅም ስለሌለው ነው ብለው ያስባሉ። የአለምን ትርጉም የለሽህነት የምንመለከተው በገጸባህሪዎች ስለሆነ ያለፈ ታሪካቸው ምንም ጥቅም የለውም። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ደግሞ የአለምን አሰልቺነት የምንመለከተው በገጸባህሪዎች ውስጥ ቢሆንም ያልፈ ታሪካቸው ግን በከፊል ተቀምጧአል። ለምሳሌ ባል ለእንግዳ ተዋናይ እንደነበረ እና አሁን ግን ከትወና ውጪ እንደሆነ ይነግረዋል። በሌላኛው ገፅ ላይ ደግሞ ባል ስለቤተሰቡ ለእንግዳ ያጫውተዋል።

*“ባል - ተዋናይ ነበርኩ (ፋታ) ጭቅጭቅ እና ውሸት ሲሰለቸኝ ተውኩላቸው” (እንግዳ፤10)*

*“ባል - አንድ ተዋናይ ከመድረኩ ውጪ ምን ህይወት ይኖረዋል? (እንግዳው አይመልስም)*
*ከውጪ ለሚያየኝ ሰው እድለኛ እመስላለሁ፣ግን አይደለሁም።...........” (እንግዳ፤13)*

በነዚህ ሁለት ቃለተውኔቶች ውስጥ ባል ተዋናይ እንደነበረ ነገር ግን ጭቅጭቅ እና ውሸት ስለሰለቸው ሙያውን እንደተወው እና ለሚመለከተው ሰው እድለኛ እና ደስተኛ የሚመስል በህይወቱ ግን ደስታ የራቀው እንደሆነ ለእንግዳ ያጫውተዋል። የሰው ልጅ የህይወትን አብዘርድነት ሲረዱ የተለያዩ የመፍትሔ ሀሳቦችን ይጠቀማሉ። ከነዚህ የተለያዩ የመፍትሔ ሀሳቦች መካከል ባል አንደኛውን የመፍትሔ ሀሳብ ይጠቀማል። ይህም ተዋናይ መሆን ነበር። “እንደ አብዘርዲስቶች እምነት ተዋናይ መሆን ማለት በተለያዩ የኪነጥበብ ስራዎች ውስጥ ተዋናይ በመሆን በገሀዱ ዓለም ያጡትን የህይወትን ትርጉም ሰዎች በገፀባሪዎቻቸው ውስጥ ይፈልጋሉ።” ባልም ተዋናይ ነበር ነገር ግን የሚመኘውን እና የሚፈልገውን ህይወት በገፀባሪዎች ውስጥ ሊያገኝ አልቻለም ጭራሽ አሰልቺ ይሆንበታል። ባል የኪነጥበብ ባለሙያ በመሆን ያጣውን እውነት እና የህይወትን ትርጉም በገፀባህሪዎች ውስጥ በመፈለግ በገሀዱ አለም ያጣውን እውነት በምናቡ ለማግኘት ከአብዘርዳዊ ህይወት ለመውጣት እንደማምለጫ ሲጠቀመው ይስተዋላል። ነገር ግን የሚያውቃቸው የኪነጥበብ ሰዎች ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው የሚናገሩት ሁሉ የፈጠራ ወሬ ሲሆንበት ሙያውን ለመተው አንድ ምክንያት ይሆነዋል።

ባል ለእንግዳ የትዳር አጋሩን ሚስትን እንዴት ተገናኝተው እንዳገባት ለእንግዳ የሚተርክለት ሲሆን ይህ ታሪክ ግን ትክክለኛ የሚስት እና የባልን ግንኙነት የሚገልፅ አይደለም። ባል ለጨዋታ የፈጠረው የሀሰት ታሪክ ነው። ባል ሚስትን እንዴት እንዳገኛት ከዚህ በታች እንዲህ ሲል ይተርክለታል....

*"ባል -.... እጮኛ ነበረችኝ። በመሀሉ እችኛዋ ትወደኛለች...ከመሬት ተነሰታ። መልኳን እንኳን ሳላውቀው ነው*

*"እሱን ካላገኘሁ እራሴን እገላለሁ!" ማለቷን ጓደኞቿ የነገሩኝ።ለመኑኝ መውጫ መግቢያ አሳጡኝ።*

*ምናልባት ለጥቂት ቀን ከተገናኘን ይተዋታል በማለት ላገኛት ተስማማሁ።*

*እንግዳ - (ፋታ) እጮኛህስ?*

*ባል - ለእሷማ አልነገርኳትም፣ተደብቄ ነው ላገኛት የተስማማሁት። ይህችኛዋ ግን እየባሰባት ሄደ።*

*ጭራሽ በጮኛዬ መቅናት ጀመረች። "የምጣዱ ሳለ...." ነው የሚባለው? እና መሸሽ ጀመርኩ።*

*ሁኔታዬ ሲገባት ራሷን አትሰቅል መሰለህ?!*

*እንግዳ - (በድንጋጤ) ተውንጂ*

*ባል - (ፈገግ ይላል) ሰዎች ደርሰው ባያድኗት ኖሮ እስከወዲያኛው ተሰናብታ ነበር። በመጨረሻ*

*"ምንድነው የምትፈልጊው?" ብዬ ጠየኳት፣"አንተን ማግባት!" ብላኝ አረፈችዋ። በጉዳዩ*

*ብዙዎች አሰብኩበት፣አወጣሁ፣አወረድኩ...."ለዚያውስ ሴት ሴት ናት፣ይቺን አገባሁ ያቺን*

*ምን ለውጥ ያመጣል?" ብዬ አገባኋት።" (እንግዳ፤13)*

ከላይ የተጠቀሱት ቃለተውኔቶች ባል ለእንግዳ ያለፈ ታሪኩን እና አሁን ያለበትን ሁኔታ ነው የተረከለት። ነገር ግን ባል ሚስቱን እንዴት እዳገኛት የተረከለት የፈጠራ ታሪክ ነው። ነገር ግን ሚስት እና ባል እዴት እደተገናኙ የሚገልጽ በተውነቱ ውስጥ አንዳች ቦታ የለም። እስከ ተውኔቱ ማብቂያ ድረስ እዴት እድተገናኙ የሚገልጽ ማስረጃ የለም። በእንግዳው ፊት ይፈጥሩት የነበረው ክርክርና ፀብም የውሸት እና የማስመሰል ነበር።

*"ሚስት -.... ሁለት ስትሰብ አይቻለሁ!*
*ባል - ዝም ብለሽ ተጫወቺ*
*ሚስት - አልጫወትም (ካርታዋን እላዩ ላይ ትበትንበታለች፣ባል በጥፊ ሲመታት ሮጣ ወደ*
*ውስጥ ትገባለች....) (እንግዳ፤16-17)*

*ሚስት - እንዳትጠጋኝ /ይቆማል/ እንዴት እንደምጠላህ ባወክ! ጨካኝ ሆነህ ጨካኝ አረከኝ፣*

*አውሬ ሆነህ አውሬ አደረከኝ፡፡ እስካሁን ለፈፀምኩት በደል ለራሴ እንኳ ይቅርታ የለኝም፡፡*

*ባል - ጥሩ፣ ይህን ያህል ከጠላሸው ማርዬ፣ ሁለተኛ አንጫወትም፡፡ (ፋታ) ከዚህ የተሻለ ሌላ ጨዋታ እንፈጥራለን፡*

*ሚስት - ምንም አይነት ጨዋታ አልፈልግም፡፡" (እንግዳ፤28)*

ይህን ያደረጉበት ምክንያት ባል እና ሚስት አሰልቺ ህይወታቸውን ለመርሳት፣ደስታ የራቀው ህይወታቸውን በደስታ ለመሙላት፣ድግምግሞሽ የበዛበት ህይወታቸውን በአዳዲስ ነገሮች ለመተካት ብለው በየቀኑ እንግዳ እየጋበዙ በእንግዳ ላይ ይጫወቱ ነበር። ይህን ሀሳብ በታሪኩ ውስጥ እንደ ሚከተለው ተገልጿል…

*"እንግዳ - /መናገር ያቅተዋል/ እ . . . እስካሁን ያወራነውን ሁሉ . . . ሆን ብላችሁ ያዘጋጃችሁት ነው ማለት ነው?*

*ባል/ሚስት - (አንድ ላይ) ላንተው ስንል!*

*እንግዳ - ሊገባኝ አይችልም*

*ሚስት - እውነቴን ነው ምልህ እስከ ዛሬ ከጋበዝናቸው እንግዶች እንዳንተ የተዋጣለት ማንም የለም፣ ልትኮራ ይገባሀል፡፡ ልብህ እንደልጅ ንጹህ ስለሆነ ማንኛውንም ነገር እንድታምን ለማድረግ አያስቸግርም፣ አንዳንዶች በጣም ተጠራጣሪ ስለሆኑ ጨዋታው ገና ሳይጀመር ያበላሹታል፡፡" (እንግዳ፤26-27)*

ከላይ በተገለፁት ቃለተውኔቶች ውስጥ ባል ከሚስቱ ጋር ተጣልቶ በጥፊ የሚመታት እና ሚስትን ያገኘበት መንገድ እና ሌሎች የተወያዩዋቸው አንዳንድ ሀሳቦች የፈጠራ ታሪክ እንደሆኑ ከላይ ያለው ቃለተውኔት ግልጽ ማሳያ ነው።

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ የሚቀረፁት ገፀባሕርያት የተለመደ ሰወኛ ባህሪያቸውን ወደ ጎን በመተው ግራ በሚያጋባ ምናልባትም በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ እብድ ተብሎ ሊጠራ የሚያስችል አይነት ማንነት እና ስብእናን ተላብሰው ሊቀርቡ ይችላሉ። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ደግሞ ይህንን ሀሳብ ጎልቶ እንመለከተዋለን። ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ቃለተውኔት ውስጥ ባልን እብድ ሊያሰኙ የሚችሉ ባህሪያት ተፈፅሟል።ህይወት ስለሰለቻቸው ብቻ በቤታቸው ውስጥ እንግዳ ጋብዘው በእንግዳው ላይ መጫወት እንዲሁም የውሸት ታሪኮችን እየነገሩ ሰውን ማሳመን እብድ ሊያሰኝ ይችላል። ይህን የባልን እብደት ሌላው የሚያጠናክረው ደግሞ በገፅ 37 ላይ......

*"ባል - /ፋታ/ እስከዛሬ ያልሞከርነውን አንድ ጨዋታ ላሳይሽ? ሚስት በመስማማት ራሷን ትነቀንቃለች፣*

*ባል ሽጉጡን ያነሳና ጥይቶችን ያወጣል፣አንድ ጥይት መልሶ ይከትና ማጋዚኑን ያሽከረክረዋል)*

*አሁን እዚህ ውስጥ ያለው ጥይት አንድ ብቻ ነው። ጥይቱ የት ቦታ እንዳለ ሳታዩ ራስሽ ላይ መተኮስ ነው ጨዋታው" (እንግዳ፤37)*

ከአብዘርድ ገፀባሕርያት መለያ ከሆኑት አንዱ የገፀባሪዎቹ ስም አልባነት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት አብዘርዲስቶች ያለፈም ይሁን የወደፊት ታሪክ ስለሌላቸው ህይወታቸው ድግምግሞሽ ስለሆነ ስማቸው በህይወታቸው ላይ የሚያመጣ አንዳች ለውጥ የለም። ስለዚህ የገፀባህሪዎች ስምም ትርጉም የለሽ ነው። ይህንን ሀሳብ በእንግዳ ተውኔት ውስጥ አጥኚው እንደሚከተለው ይተነትነዋል።

*" ባል - መቼም ባለቤቴ መጥታ እስክታስተዋውቀን ድረስ መጠበቅ ያለብን አይመስለኝም። እራሳችን*

*መተዋወቁ የግድ ይሆናል (መነፀሩን ያወልቅና እጁን ይዘረጋለታል)*

*እንግዳ - (ግር እያለው ይጨብጠዋል) እንግዳ...." (እንግዳ፤10)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ ባል እና እንግዳ ስማቸውን ሲጠቅሱ አይስተዋልም። አንድ ህይወት የሰለቸው ሰው ስሙን ቢናገር በህይወቱ ላይ አንዳች ለውጥ አይከሰትም እና ባልም ያደረገው ይህን ድርጊት ነው።

ስም ማንነት ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ነው። ስም ቤተሰቦቻችን በአንድ ወቅት ታላቅ ስራን ሰርተው ባለፉ የሀይማኖት ሰዎች፣የጦር ሜዳ ጀግኖች፣በሚወዷቸው አርቲስቶች ስም ሊጠሩ ይችላሉ። ስም በጊዜው የነበረውን ማህበራዊ ሁኔታ ሊገልፅ ይችላል። "ስምን መላዕክ ያወጣዋል" ይባላል። ይህ ማለት ስም እና ምግባር ሲገጣጠም መሆኑ ነው። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ግን ባል ስሙ ሲገለፅ አይስተዋልም። የባል ምግባሩ እንጂ ስሙ የለም። ምግባሩ ደግሞ ህይወት ስለሰለቸው ብቻ በቤቱ ውስጥ እንግዶችን እየጋበዘ በእንግዶች ላይ መጫወት ነው።

## ሚስት

አጥኚው የሚስትን አጠቃላይ የገፀባህሪ አሳሳል ከአብዘርድ የቴአትር መለያ ባሪያት አንፃር እንደሚከተለው የሚተነትን ነው።

በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ከሚገኙት ሶስት ገፀባህሪዎች ውስጥ ሚስት አንዷ ናት። አካላዊ አሳሳሏ ቆንጆ ስትሆን፣ፆታዋ ሴት ከመሆኗ እና ትዳር እንዳላት ከተገለፀው ውጪ ስለቤተሰቧ፣ስለሙያዋ፣ ስለትምህርቷ፣ስለሃይማኖቷ፣ስለሀብት መጠኗ በአጠቃላይ ስለማንነቷ ምንም የተጠቀሰበት መንገድ የለም።

*ሚስት - እንከን የማይወጣለት ቆንጆ ናት*

*እንግዳ - በመልክ ቢሆን ኑሮ ከሷ ይልቅ አንቺን ነበር የምመርጠው (እንግዳ፤3)*

በዚህ ቃለ ተውኔት ውስጥ የሚስትን ቁንጅናን መረዳት ይቻላል። ሚስትም ልክ እንደ ባል ወደ ቤቷ እንግዳን ከጋበዘችው በኃላ አሁን ሚስቴ እያለ የሚጠራት ወንድ ባሏ እንዳልሆነ እና ስለቤተሰቧ አኗኗር ለእንግዳ ትተርክለታለች። እነዚህ ትርክቶች ግን የሚስትን እውነተኛ ማንነት የሚገለፅ ሳይሆን አሰልቺ የሆነ ህይወቷን ለመርሳት ከባሏ ጋር የዘየደችው የፈጠራ ታሪክ ነው። ይህንን አጥኚው በማስረጃ የሚተነትን ይሆናል።

*እንግዳ - ታዲያ እንዴት ነው የተጋባችሁት?*

*ሚስት - አልተጋባንም። ዝም ብለን ነው አብረን የምንኖረው።አልጋችን እንኳን ለየብቻ ነው።*

*እሱ ግን ባልና ሚስት ነን ብሎ ያምናል። አንዳንዴማ ስለሰርጋችን ቀን ሁሉ ያወራልኛል።*

*አንድ ቀን ባልና ሚስት እንዳልሆንንና በሠርግ መጋባታችንም ራሱ በሀሳቡ የፈጠረው ቅዠት*

*እንደሆነ ላስረዳው ስሞክር፣እንደ እብድ አደረገው። በሽታው ሊነሳበት ነው ተብዬ*

*ስለፈራሁ ተውኩት (እንግዳ፤20)*

ባል አማኑኤል ገብቶ እንደነበር የአምሮ በሽተኛ እንደሆነ እና ለእንግዳ የነገረው ታሪክ ሁሉ ውሸት እንደሆነ ሚስት ለእንግዳው ታስረዳዋለች። ከላይ ባል እንደተጋቡ ለእንግዳ ሲነግረው ሚስት ደግሞ እንዳልተጋቡ እና ባል ያለው ሁሉ ውሸት እንደሆነ በዚህኛው ቃለተውኔት ውስጥ ታስረዳለች።

*“ሚስት - አባቴ እኔ ሳልወለድ ነው። እኔ ከተወለድኩ በኃላ እናቴ ብዙም ሳትቆይ ባል አገባች።*

*እያደኩ ስሄድ የቤቱን ስራ ሁሉ የምሰራው እኔ ሆንኩ። ሰራተኛ መቅጠር ሳያቅታቸው እናቴ*

*እኔን ለምን እደምታሰራኝ የዛን ጊዜም ቢሆን ይገርመኝ ነበር። የበለጠ የሚገርመው ደሞ ታናሽ እህቴ አንዲት ነገር እንድትሰራ አለመፍቀዷ ነው።..". (እንግዳ፤21)*

በዚህኛው ቃለተውኔት ውስጥ ሚስት እህት እንዳላት እናቷ ጨካኝ እንደሆነች እና እንደምታሰቃያት ለእንግዳው ትነግረዋለች።ህይወት እንደዚህ ናት ለአንዱ ስትመች ለሌላው ደግሞ የእንግድነት ስሜት እንዲሰማን ታደርጋለች። በሚስትም ህይወት የተከሰተው ይህ ነው። በቤቷ ውስጥ በወለደቻት እናቷ ስትሰቃይ፣ስትገፋ ከታናሽ እህቷ በታች ስትሆን ይስተዋላል።

በነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ቃለተውኔቶች ውስጥ ሚስት ለእንግዳ ስለ አለፈ ታሪኳ ያጫወተችው ውሸት እንደሆነ እራሷ ሚስት ለእንግዳ ታስረዳዋለች። ይህን ያደረገችው ከባሏ ጋር ሁና አሰልቺ ህይወቷን፣ ድግምግሞሽ የበዛበት ህይወቷን፣ደስታ የራቀውን ህይወቷን በደስታ ለመሙላት እና በአዳዲስ ነገሮች ለመተካት ብላ በየቀኑ ከባሏ ጋር በመማከር እንግዳ እቤታቸው ውስጥ እየጋበዙ በእንግዳው ላይ ይጫወቱበት ነበር። ይህን ሀሳብ በታሪኩ ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጿል።

"*ሚስት* - ሁለቱ ባልና ሚስት ናቸው፡፡ ኑሮ በጣም የሰለቻቸው፡፡
*ባል* - አንድ ቀን ጊዜውን ለማሳለፍ ምን ቢያረጉ እንደሚሻል ሲወያዩ አንድ ሃሳብ መጣላቸው፣
*ሚ* - እውነተኛ ቲያትር መሥራት!..............." *(እንግዳ፤26-27)*

ሚስት ለእንግዳ ስለቤተሰቦቿ ስለባሏ ታሪክ እንዲሁም ሌሎች ያወሯቸው ለርዕሰ ጉዳዮች ሁሉ ውሸት እንደሆነ በነዚህ ቃለተውኔት ማረጋገጥ ይቻላል።እነዚህ ሁለት ባል እና ሚስት የህይወትን አሰልቺነት እና የህይወትን ትርጉም የለሽነት ቢረዱም አምነው መቀበል ግን ስላልቻሉ በየቀኑ አዳዲስ እንግዶችን እየጋበዙ አዳዲስ ታሪኮችን እየፈጠሩ እራሳቸውን በተመረጡ ነገሮች ይጠምዱ ነበር።

በአብዘርድ ተውኔቶች ውስጥ የሚቀረፁት ገፀባሪያት የተለመደ ሰወኛ ባህሪያቸውን ወደ ጎን በመተው ግራ በሚያጋባ ምናልባትም በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ እብድ ተብሎ ሊጠራ የሚያስችል አይነት ማንነት እና ስብእና ሀሳብ ጎልቶ እንመለከተዋለን። ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ሀሳብ ውስጥ ሚስት እብድ ሊያሰኙ የሚችሉ ድርጊቶችን ፈፅማለች።

ህይወት ስለሰለቻት ብቻ በቤቷ ውስጥ እንግዳ ጋብዛ በእንግዳው ላይ መጫወት እንዲሁም የፈጠራ ታሪኮችን እየነገሩ ሰውንም ማሳመን እብድ ሊያሰኝ ይችላል። ሌላው የሚስትን እብደት የሚያጠናክረው ደግሞ በገፅ

16 ላይ ሚስት ባል እና እንግዳ ካርታ ይጫወታሉ። የተሸነፈው የሚቀጣውን ማንኛውም ቅጣት ለመቀበል ሶስቱም ይስማማሉ። በጨዋታው መሀልም ሚስት ትሸነፍ እና ባል ሚስትን ልብሷን እንድታወልቅ ያዛታል። ሚስትም ቀስ እያለች ጫማውን ታወልቃለች ልብሷን ልታወልቅ ስትል ባል እንግዳውን "ቅጣቱ ይክበድ ወይስ ይቅለል" እያለ ሲያማክረው ሚስት ጫማዋን አጥልቃ ትመለሳለች። አጥኚው በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ የተረዳው አብዛኛው ሰው በእንግዳ ፊት እርቃኑን መቆም ይቅር እና ቲሸርት ለመቀየር እሺ የሚል ለማግኘት ይከብዳል። ሚስት ግን ገና ማንኛውም ቅጣት ሲባል ተስማምታ በሁለት ወንዶች መካከል ተጫውታለች። ቅጣቷን ለመፈፀም ተነስታ ሞክራ ነበር። ሌላው የሚስትን እብደት የምንመለከተው ገፅ 37 ላይ ባል አቀባብሎ እራሱ ላይ ሊተኩስ የፈራውን ነገር እሷ ተቀብላ ያለምንም ማመንታት ወደ ራሷ ትተኩሰዋለች።

**እንግዳ**

በእንግዳ ተውኔት ውስጥ የሚገኘው ሌላኛው ገፀባህሪ "እንግዳ" ይሰኛል። የእንግዳን የገፀባህሪ አሳሳል አጥኚው ሲመለከት ከአብዘርድ ገፀባህሪ አሳሳል ይልቅ ዘልማዳዊ ወደሆነው የገፀባህሪ አሳሳል የተጠጋ ነው። የእንግዳን የገፀባህሪ አሳሳል አጥኚው ሲመለከተው ያለፈ ታሪኩ ቤተሰቡ፣የፍቅር ህይወቱ፣ሙያው፣ የትምህርት ደረጃው በግልጽ የተቀመጠ ነው። ይህ ደግሞ ከአብዘርድ የተውኔት ገጸባህሪያት አሳሳል አንጻር አጥኚው ሲመለከተው የአብዘርድን ባህሪያት የማያሟላ ሁኖ አግኝቶታል። እንግዳ ገጸባህሪው የቀረበበት መንገድ ከገጸባህሪያት አሳሳል አንጻር መግለጽ ይቻላል። ይህን ደግሞ ከዚህ በታች የቀረቡት ማስረጃዎች ግልጽ ማሳያዎች ናቸው።

*“ሚስት - አግብተሃል ማለት ነው?*

*እንግዳ - አላገባሁም ከሁለት እህቶቼ ጋር ነዉ የምኖረው" (እንግዳ፤23)*

እንግዳ የተሰኘው ገፀባህሪ ሁለት እህቶች ያሉት እና ያላገባ ነው። እንግዳ እጮኛ እንደነበረው እና በሱላይ ሌላ ወንድ ስለደረበችበት እንደተዋት ለሚስት ያጫውታታል። ይህን ሀሳብ ከዚህ በታች የቀረበው ቃለተውኔት እንዲ ሲል ያጠናክረዋል

*“እንግዳ - ሁለመናሽ የበፊቷ እጮኛዬን ነው የሚመስለው.... ለማንኛውም መጨረሻ ላይ ተለያየን*

*ሚስት - ምን ሆናችሁ?*

*እንግዳ - ከሌላ ሰው ጋር መውጣቷን ደረስኩበት።” (እንግዳ፤23)*

እንግዳ ሙያው እና የትምህርት ደረጃው የተገለፀ ነው።

*"ባል - ለመሆኑ ያንተ ሙያ ምንድነው?*

*እንግዳ - የስነ-ልቦና ሀኪም ነኝ" (እንግዳ፤12)*

በዚህ ቃለ ተውኔት ውስጥ እንግዳ የስነልቦና ሀኪም ሲሆን የስነልቦና ሀኪም ለመሆን በቅድሚያ የዩኒቨርሲቲ ምሩቅ መሆን ያስፈልጋል። እንግዳም የዩኒቨርሲቲ ምሩቅ እና የስነልቦና ሀኪም ነው ማለት ይቻላል።

እንግዳ ሰውን በቀላሉ የሚያምን ማፍቀር የሚችል እና ለመርዳት ወደኃላ የማይል ነው።

*"ሚስት - እውነቱን ነው የምልህ እስከ ዛሬ ከጋበዝናቸው እንግዶች እንዳንተ የተዋጣለት ማንም*

*የለም ልትኮራ ይገባሀል። ልብህ እንደ ልጅ ንፁህ ስለሆነ ማንኛውም ነገር እንድታምን*

*ለማድረግ አያስቸግርም...." (እንግዳ፤27)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ ሚስት የእንግዳን የዋህነት እና ሰዎችን በቀላሉ ማመኑን ትመሰክራለች።ከዚህ በተጨማሪ የነገሩት ነገር ሁሉ ውሸት እንደሆነ እያወቀ እንኳን ሚስትን ለመርዳት ሲሞክር ይስተዋላል።

*"ሚስት - አብሬህ ስቀመጥ ምንህ እሆናለሁ? ገረድህ?*

*እእንግዳ - አረ እኔ እንደዛ አላሰብኩም*

*ሚስት - ታዲያ ምንድነው ያሰብከው?*

*እእንግዳ - ልክ እንደእህታችን መኖር ትችያለሽ" (እንግዳ፤31)*

*ሚስት - ለምን? ለምንድነው ለኔ ደግ የሆንክልኝ?*

*እእንግዳ - ስላሳዘንሺኝ ነዋ፣ በዛ ላይ አሁን የምትሄጂበት የለሽም(እንግዳ፤32)*

በነዚህ ሁለት ቃለተውኔቶች እንግዳ በባል እና በሚስት ጨዋታ እንደተሸወደ አውቆ አሰልቺ ህይወታቸውን መርሻ እንዳደረጉት ገብቶት የእሱን ጊዜ ገንዘቡን አባክነውበት እንኳን ሚስትን አብራው እንድትኖር እና ልክ እደህቱ እንደሚያት እና ሊረዳት እንደሚፈልግ ምርጫ ያቀርብላታል፡፡

በአጠቃላይ የእንግዳን ገፀባህሪ አሳሳል አጥኚው ሲመለከተው ዘልማዳዊ የገፀባህሪ አሳሳል ያለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡ እንግዳ ያላገባ፣ሁለት እህቶች ያሉት፣የስነልቦና ባለሙያ፣የተማረ እና ሰው አክባሪ ነው፡፡

በአብዘርድ ተውኔቶች ውስጥ ገፀባሪያቱ ድርጊቱ በሚከናወንበት ቦታ እና ጊዜ ለመገናኘት ያበቃቸው ምክንያት ሳይገለፅ ዝም ብለው ይገናኙ እና ተውኔታዊ ድርጊቱን ይከውናሉ፡፡ በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ባል እና ሚስት እንዴት እንደተገናኙ የት እደተዋወቁ መቼ እንደተጋቡ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ተውኔታዊ ድርጊያውን ለመከወን ያገናኛቸው ምክንያት ባለትዳር መሆናቸው ነው፡፡ እንግዳ ግን ተውኔታዊ ድርጊያውን ለመከወን የተገኘበት ምክንያት በባል እና በሚስት ጨዋታ ውስጥ እንግዳ ምንም ሳያውቅ እና ሳይረዳ ተጋባዥ እንግዳ በመሆን ሲሆን ከባል እና ከሚስት ጋር ያለው ግንኙነት በግልፅ የተቀመጠ ነው፡፡

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ደራሲው ገፀባሪያቱ አብዘርዳዊነታቸውን በደንብ ይገልፅለት ዘንድ ለህይወት እና ለማህበረሰቡ ያላቸውን ስሜት አልባነት እና ተስፋቢስነታቸውን በደንብ ይቀርፃቸዋል፡፡ በእንግዳ ተውኔት ውስጥም የባል እና የሚስት ተስፋቢስነት እና ለህይወት ያላቸውን አመለካከት አጥኚው ከላይ የዳሰሰው ነው፡፡ አብዘርዳውያን ለማህበረሰቡ ያላቸውን ስሜት አልባነት በባል እና በሚስት ውስጥ ተመልክቶታል፡፡ እነዚህ ሁለት ባል እና ሚስት በየጊዜው አንድ አንድ እንግዳ በሚጋብዙበት ወቅት እንግዳው የሚያባክነው ጊዜ፣ገንዘብ እና ጉልበት ምንም ሳይመስላቸው በየጊዜው የተለያዩ እንግዶችን ይጋብዙ ነበር፡፡ በቤታቸው ውስጥ ከጋበዙት በኃላ በሚፈጥሩት የውሸት ታሪክ እንግዳውን ለሁለት ከፍለው ያስጨንቁት ነበር፡፡አጥኚው በደረሰበት መደምደሚያ የእንግዳው ገፀባህሪ በተውኔቱ ውስጥ የተካተተው በአብዘርድ እሳቤ ውስጥ ያሉ ሰዎች ለማህበረሰቡ ግድ እንደሌላቸው እንደ ማሳያ የቀረበ እንደሆነ ያምናል፡፡

አብዘርዲስቶች ከሚጠቀሙባቸው የመፍትሔ ሀሳቦች መካከል እራሱን በሌላ ነገር መጥመድ አንዱ ነው፡፡ ለምሳሌ ቅንጡ ነገሮችን በማድረግ፣ውድ ምግቦችን በመመገብ፣ውድ የሆኑ እቃዎችን በመግዛት፣ጨዋታዎችን በመጫወት እራስን በነዚህ ነገሮች አብዘርዲስቶች ይጠምዳሉ፡፡ ባልም በቤቱ ውስጥ እንግዳ ጋብዞ አሰልቺ የሆነ ህይወቱን ለመርሳት በእንግዶች ላይ የተለያዩ ጨዋታዎችን ከሚስቱ ጋር አንድ ላይ በመሆን እራሳቸውን በጨዋታዎች ይጠምዳሉ፡፡

ሌላኛው የአብዘርዲስቶች የመፍትሔ ሀሳብ የህይወትን አብዘርድነት አምኖ መቀበል ነው፡፡ በዚህ እሳቤ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው የህይወትን አብዘርድነት አምኖ ተቀብሎ ደስታን ለማግኘት መሞከር አለበት ብለው ይመክራሉ፡፡ ባል ተዋናይ በመሆን እና ሀሳብን በሌሎች ነገሮች ሲጠምድ ሚስትም ልክ እንደባል ሚስትም

እነዚህን የመፍትሔ ሀሳቦች ቢጠቀሙም ሊሳካ አልቻለም። ስለዚህ የህይወትን ትርጉም አልባነት አምነው እውነታውን በመቀበል ደስተኛ ለመሆን ባል እና ሚስት እራሳቸውን ያሳምናሉ።

በእንግዳ ተውኔት ውስጥ የገፀባሪያቱን የወደፊት እጣፈንታ ማውቅ አይቻልም። ባል እና ሚስት በእያንዳንዱ ድርጊታቸው ውስጥ ቀጥሎ ምን ያደርጋሉ ብሎ መገመት አይቻልም። ምክንያቱም እነዚህ ህይወት ያሰለቻቸው ሁለት ባል እና ሚስት ወደፊት ምንም ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ። ነገር ግን በእርግጠኝነት ይህን ያደርጋሉ ብሎ መናገር አይቻልም። በእንደዚህ አይነት ህይወት ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው ምን ሊያደርግ እንደሚችል የሚታወቅ ነገር የለም።

## 3.2.2 **"የእንግዳ" ተውኔት መቼት ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላሉ**?

የአብዘርድ መቼት ዘልማዳዊ ከሆነው የመቼት አገላለፅ የተለየ ነው። አጥኚው በምዕራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደሞከረው በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ጊዜውም ቦታውም ማህበራዊ እውነታውም ላይታወቅ ይችላል። ለዚህም ምክንያት በሰው አካል፣በሰው አካል፣እና በሰው አምሳል የሚቀረፀው ገፀባህሪ ትርጉም የለሽ ተደርጎ ስለሚወስድ ነው።

ሁለት ባል እና ሚስት ትርጉም ያጣውን ህይወታቸውን፣ድግግሞሽ የበዛበትን ህይወታቸውን ለመርሳት እንግዳ ጋብዘው በእንግዳው ላይ ሲጫወቱ እንመለከታለን። ተውኔቱ ሲጀመር አጠቃላይ መቼቱ የት እንደሆነ እና አጠቃላይ የተውኔቱ ጊዜውም መቼ እንደሆነ አይታወቅም። ውስን ቦታው በባል እና በሚስት የወይን ተክል ግቢ ውስጥ ሲሆን ውስን ጊዜው ደግሞ ምሽት ላይ ነው።

*"…. መካከለኛ ደረጃ ሆኖ የወይን ተክል ያለው ግቢ ይታያል።"(እንግዳ፤1)*

በአብዘርድ ትውኔቶች ውስጥ  መቼቱ በአብዛኛው አንድ የተወሰነ የማይቀየር ቦታ ላይ ያርፋል፡፡ በእንግዳ ተውኔት ውስጥም በባል ቤት ውስጥ ስሆን ከዛ ውጪ ቦታው አይቀየርም እስከ መጨረሻው በዚሁ በባል ቤት ውስጥ ነው የሚጨርሱት።

እንግዳ ተውኔትን በዘልማዳዊ ከሆነው የመቼት ማህበራዊ እውነታ አንፃር አጥኚው ሲመለከተው የባል እና የሚስትን የትምህርት ደረጃ ብልፅግና ድህነት፣አመጋገባቸው፣እምነታቸው ምን እንደሆነ የሚገልፅ ቦታ

የለም። ይህ ደግሞ የሆነበት ምክንያት ገፀባሪያቱ የሚሳሉት ትርጉመ ቢስ ተደርገው ቢሆኑም በሂወታቸው ውስጥ አንዳች ትርጉም ለማገኘት ሲፍጨረጨሩ ነው የሚስተዋለው። በእንግዳ ተኔት ውስጥም ማህበራዊ ሁኔታው አብሮ ትርጉም የለሽ ተደርጎ ነው የተሳለው። ይህ የሆነበት ምክንያት ገፀባህሪያቱ ሃይማኖታቸው የሚገለፅ ከሆነ የሚያምኑት አምላክ አላቸው ማለት ነው። ሀይማኖት አላቸው ማለት ደግሞ የፈጣሪያቸውን ቃል ይሰማሉ። ቃሉን አዳምጠው አምነው በቃሉ የሚኖሩ ከሆነ የሚደሰቱ ይሆናሉ ማለት ነው። የየገፀባህሪያቱ የሀብት መጠን ተገለፀ ማለት ገፀባህሪው ምናልባት እራሱን ለማስደሰት በገንዘቡ ቁሳዊ በሆኑ ነገሮች እራሱን ለማስደሰት በገንዘቡ ቁሳዊ በሆኑ ነገሮች እራሱን ለማስደሰት ይጥራል።
በአብዘርድ ፅንሰ ሀሳብ የሚኖር ሰው ግን አምላኩን በሚጠይቀው ጥያቄ ምላሽ ሲያጣ ባለው ገንዘብ መደሰት ሳይችል ሲቀር በዙሪያው ባለው ሰው መደሰት ሳይችል ሲቀር ጭንቀት ውስጥ ይገባል።

አብዘርዲስቶች እንደሚያምኑት በአለም ላይ አዲስ ነገር የለም ህይወት አሰልቺናት ጨለማ በበዛበት አለም ውስጥ ብርሃንን ነው የሚፈልጉት። ይህን ሃሳባቸውን ለመግለጽ መቼት አንዱ ነው። አዲስ ነገር የለም ህይወት አሰልቺናት የሚለውን ለመግለጽ መቼቶቹ እንደ ዘልማዳዊ የመቼት አገላለጽ በስርአት አይገለጹም። በእንግዳ ተውኔት ውስጥም ተእይንቱ ሲጀመር ባል ጨለማ ውስጥ ተቀምጦ ነው።

*ሚስት _ ለምን ጨለማ ውስጥ ተቀመጥክ?*

*ባል _ እዚህ ግቢ ምን የሚታይ አዲስ ነገር አለ? በግቢው ያለውን እያንዳንዱን አትክልትና የተቀመጠበትን ቦታ እራሴን ከማውቀው በላይ አውቀዋለሁ። ታዲያ መብራቱ ምን ያረግልኛል? (እንግዳ፤1)*

### 3.2.3 “የእንግዳ” ተውኔት ቃለተውኔት ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላል?

የአብዘርድ ቃለተውኔት ዘልማዳዊ ከምንለው የቃለተውኔት አይነት የሚመደብ አይደለም። አጥኚው በምዕራፍ ሁለት እንደገለፀው ገፀባህሪያት እርስ በርስ የሚለዋወጡት ንግግር በአንዱ ቅንጣት ታሪክ ያለው ንግግራቸው በቀጣዩ ቅንጣት ታሪክ ያለው ንግግራቸው በቀጣዩ ቅንጣት ታሪክ ከሚገኘው ንግግራቸው ጋር የጠበቀ ግንኙነት የለውም። ገፀባህሪያቱ በሚናገራቸው ቃለ ተውኔቶች ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተ ነገሮች ሰዋሰዋዊ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ አይደሉም።በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ገፀባሪያቱ እርስ በርስ የሚለዋወጡት ንግግር በአንዱ ቅንጣት ታሪክ ያለው ንግግራቸው በቀጣዩ ቅንጣት ታሪክ ጋር ምን የጠበቀ ግንኙነት የላቸውም። ይህን ሀሳብ የሚያጠናክርልን ደግሞ

*“ ሚስት - በጣም ይቅርታ ከመጣህ ቆየህ?*

*እንግዳ - አይ ብዙም አልቆየሁም። በዛ ላይ ከባለቤትሽ ጋር እየተጨዋወትን ስለነበር....*

*ባል - ፍቅርዬ፣ አይገርምም የሶስታችን መገናኘት*

*ሚስት - እንዴት ማለት;*

*(ባል ከኋላው ደብቆት የነበረውን የንግዳን አበባ ያወጣና ይሰጣታል)*

*ሚስት - ዋው፣ (ለንግዳ እያሳየችው) የሚያምር አበባ ነው አደል!*

*እንግዳ - እ . . . አበባው*

*ሚስት - እ?*

*ባል - ልክ ካርታ ልንጫወት ስንል ነው የመጣሺው ከፈለግሽ ግቢበት*

*ሚስት - ጥሩ" (እንግዳ፤15)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ ሶስት ጥቃቅን ታሪኮች ሲኖሩ ሶስቱ ጥቃቅን ታሪኮች ሳይቋጩ ወደ አራተኛው ቅንጣት ታሪክ ይገባሉ። ሚስት እንግዳን ከመጣህ ቆየህ ብላ መቆየቱን እና አለመቆየቱን ስትጠይቀው ባል ደግሞ መገናኘት በመገረም ይጠይቃታል ይህ ሀሳብ ሳይጠናቀቅ ባል ለሚስት አበባ ይሰጣታል ወሬው ወደ አበባ ይቀየራል የአበባውን ሳይጨርሱ ባል ወሬውን ወደ ካርታ ጨዋታ ይመራዋል። እነዚህ ቅንጣት ታሪኮች አንዳቸው ከአንዳቸው ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም።

በአብዘርድ ተውኔቶች ውስጥ ገፀባህሪዎቹ አንዳንዴ ያልተጠየቁትን ወይም ከመጀመሪያው ሀሳብ ጋር የማይገናኝ መልስ ይመልሳሉ።

*"ባል- መቼም እግሯ ላይ ወድቄ አለምናትም*

*ሚስት - እርግጠኛ ነህ?*

*ባል - ለምን ጠየቅሽኝ?*

*ሚስት - ዝም ብዬ ነው*

*ባል - ዝም ብለሽማ አይሆንም ምን ያሰብሺው ነገር አለ?*

*ሚስት - ቲያትር ቤት ያገኘሁትን ሰውዬ የሆነ ቦታ የማውቀው ይመስለኛል የት እደሆነ*

*ግን ማስታወስ አልቻልኩም አያውቀኝም እደሆነ ስጠይቀው ደሞ ካደኝ" (እንግዳ፤4)*

ባል የጠየቀው ያሰብሺው ምንድነው ሲሆን ሚስት የመለሰችው ግን ቲያትር ቤት ያገኘችውን ሰው የት እንደምታውቀው ባልን ትጠይቀዋለች።

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ በማህበረሰቡ ዘንድ ፀያፍ የሚባሉ ቃላቶችን እና ድርጊቶችን ሊያደርጉ ይችላሉ። በእንግዳ ተውኔት ውስጥም ፀያፍ የሆነ ድርጊት ሲፈፅሙ ይስተዋላል።

*"ሚስት - ለምን መጀመሪያ አንተ አትነግረኝም? (ፀጥታ። ሰስፔንስ ያለው ሙዚቃ እየተሰማ፣አትኩሮ ካያት በኃላ፣ በዝግታ ይጠጋታል፣አንገቱን ሰገግ አድርጎ አይኗ ውስጥ ያያል፣መለስ ብሎ ቁመናዋ እያጠና ከኃላዋ ይዞር እና አንገቷ ስር ተጠግቶ ያሸታታል። በዚህ ሁሉ ጊዜ ሚስት እንዳልተመቻት ይታያል። በዝግታ እጇቿን ወደላይ ያነሳ እና ይፈትሻል፣ጡቷን ያዝ ሲያደርግ እንደመዘግነን ይላታል፣እሱ ግን ፈገግታ ይላል፣እግራ ድረስ ወርዶ ሲመለስ አንዱን እግሯን ለብቻ ይዞ ወደላይ ይወጣና በቀሚሷ ስር ትንሽ ሄዶ ያቆማል) ለምን አቆምክ?*

*ባል - ልቀጥል?*

*ሚስት - ቀጥል!" (እንግዳ፣2)*

አብዘርዲስቶች እነዚህን በማህበረሰቡ ዘንድ ፀያፍ ተብለው የተፈረጁትን የሚፈፅሙበት ምክንያት ህይወት ትርጉም የላትም ስለዚህ እነዚህ ፀያፍ ድርጊቶች ደግሞ አንዱ የህይወታችን አካሎች ናቸዉ ብለው ያምናሉ። ፀያፍ ድርጊት ተብለው የተቀመጡት ለማህበረሰቡ ከፈጣሪ በሀይማኖት አባቶች በኩል ሀፅያት እና ነውር ተብለው የተሰጡ ትዕዛዛት ናቸው። አብዘርዲስቶች በፈጣሪ መኖር የማያምኑ፣ፈጣሪ ቢኖር የሰው ልጅ ህይወት ትርጉም አልባ አይሆንም ብለው የሚያስቡ ናቸው። የእኛን መኖር የረሳው ፈጣሪ ለምን ፀያፍ ወይም ሀጥያት ናቸው ተብለው ለማህበረሰቡ ይሰጣሉ? ብለው ይሞግታሉ። ስለዚህ አብዘርዲስቶች የሚያደርጉት ይህን የማህበረሰቡን አጉል እምነት ብለው የሚያስቡትን መጣስ ነው። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ባል ሚስት አንገቷ ስር ገብቶ ሲሸታት፣በተመልካች ፊት ጡቷን ሲይዝ እና እጁን በቀሚሷ ልኮ ወደ ጭኖቿ መሀል ሲዳብሳት ይህ ድርጊት በእኛ ሀገር እጅግ ፀያፍ ድርጊት ነው። ማህበረሰቡ እና ሀይማኖት ተስማምተው ያፀደቁት ነው።

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ቃለተውኔቶቹ የአብዘርድን ፅንሰ ሀሳብ የሚሸከሙ መሆን አለበት። ይህ ማለት የህይወትን አሰልቺነት፣ደስታ ማለት ምን ማለት ነው የሚሉትን ሀሳቦች በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ቃለተውኔቶቹ ተሸክመውት ይስተዋላል።

*ሚስት - ሁለት ባልና ሚስት ናቸው። ኑሮ በጣም ያሰለቻቸው*

*ባል - አንድ ቀን ጊዜውን ለማሳለፍ ምን ቢያረጉ እንደ ሚሻል ሲወያዩ አንድ ሃሳብ መጣላቸው፣*

*ሚስት - እውነተኛ ቲያትር መስራት (እንግዳ፤26)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ የባል እና የሚስት አስልቺ ህይወታቸውን መመልከት ይቻላል። ህይወት ሲሰለቻቸው ጊዜያቸውን ለማሳለፍ በቤታቸው ውስጥ እንግዳ እየጋበዙ እውነተኛ ቲያትር መስራት የሚል ሀሳብ መጣላቸው።

ሌላው ይህን ሀሳብ የሚያጠናክርልን ሚስት ለባል ይህ እንግዳ እየጋበዙ የሚጫወቱት ጨዋታ እንዲቀር የምትጠይቅበት ነው።

*"ሚስት - ከዛሬ ጀምሮ ይህ ጨዋታ ይቅር*

*ባል - ከዛስ?*

*ሚስት - ከዛማ... እኔኛ (ፋታ) ሌሎች ባልና ሚስቶች ብቻቸውን ሲሆን ምን ይሆን የሚሰሩት?" (እንግዳ፤35)*

ይህ ጨዋታ ሚስት የጀመረችበት አለማ ማለትም አሰልቺ ህይወቷን ለመርሳት ነበር ይህ ግን ሲሆን አይታይም ከዛ ይልቅ ጨዋታውም ሲሰለቻት ነው የምንመለከተው።

*"ባል - ግን ሁሌም አዲስ እንግዳ መሆን አለበት አለበለዛ አሰልቺ ይሆናል*

*ሚስት - ልክ እንደ ህይወት" (እንግዳ፤27)*

በእንግዳ ተውኔት ወስጥ ባል እና ሚስት አዳዲስ እንግዳ ነው የሚጋብዙት። ካልሆነ ግን መጀመሪያም ይህን ጨዋታ የጀመሩት ህይወት ሰልችቷቸው ነው እና አዲስ እንግዳ የማይሆን ከሆነ እንደ ህይወት ድግምግሞሽ ይሆን እና አስልቺ ይሆንባቸዋል። ከአብዘርድ ጥያቄዎች መካከል አንዱ የመፈጠርህ እና በዚህች አለም

የመገኘትህ አላማ ምንድነው የሚል ነው ይህን ሀሳብ በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ቃለተውኔቱ ተሸክሞት ይገኛል።

*"ባል - የህይወትህን ግብ ታውቀዋለህ?*

*እንግዳ - አቤት?*

*ባል - አንድ ሰው መቼም ያላንዳች ምክንያት ወደዚህ አይመጣም" (እንግዳ፤10)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ ባል ሁሉም ሰው ወደዚህ አለም ያላንዳች ምክንያት አይመጣም ብሎ ያምናል ይህን ጥያቄ ደግሞ አብዘርድ የሚያነሳው ይህን ነው። በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ቋንቋ የተወሰነ ህግ እና ስርአት የለውም። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ግን ቃለ ተውኔቶች የአብዘርድ ፅንሰ ሀሳብን የሚሸከሙ እንጂ የቋንቋ ህግና ስርዓት የሚያፈርሱ አይደለም።

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ የሚናገሩት ቃለተውኔት ተመልካችን ላይገባው ይችላል። የሚለዋወጡት ቃለተውኔት ተመልካች ዘንድ ሲደርስ ተመልካቹ ምን ለማለት ፈልጎ ነው ብለው መመራመር ይጀምራሉ። አንዳንዴ አብዘርዲስቶች ይህን የሚያደርጉት ተመልካቹ በቃለ ተውኔቱ ግራ እንደተጋቡ ሁሉ ህይወትም እንደ ቃለተውኔቱ ግራ አጋቢ ነው ለማለት ነው። በእንግዳ ተውኔት ላይም የምንመለከተው ይህን ነው።

"ባል - የኦቴሎን ታሪክ ታውቀዋለህ?

*እንግዳ* - እንግሊዝ አገር ሳለሁ ቴአትሩን አይቼዋለሁ

ባል - ጎሽ፣ የተማረ ይግደለኝ ማለት እንዲህ ነው! (ፋታ) እኔ ኦቴሎ ነኝ! እንግዲህ ታሪኩን ስለምታቀው ምን ማለቴ እንደሆነ ይገባህል፡፡" *(እንግዳ፤17)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ ተደራሲው ኦቴሎ ማን ነው? ምንድንስ ነው ያደረገው? አካላዊ አቋሙ ምን ይመስላል?ነጭ ነው ወይስ ጥቁር?ጀግና ነው ወይስ ፈሪ?የህይማኖት አባት ነው ወይስ ፖለቲከኛ? ወጣት ነው ወይስ ሽማግሌ? እያለ ሊመልሳቸው እና ሊረዳቸው የማይችለውን ጥያቄዎች እራሱን እና በዙሪያው ያለውን ተመልካች ሊጠይቅ ይችላል። ለዚህ ሁሉ ጥያቄ መልስ ሲያጣ ከህይወት ጋር ሊያገናኘው ይችላል። ህይወትም እኮ እደዚህ ናት ግራ የምታጋባ ለምትጠየቀው ጥያቄ ምላሽ የማትሰጥ ናት ብለው ያስባሉ።

በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ቋንቋዎቹ የቀረቡበት መንገድ ዘልማዳዊ ቢሆኑም የገቡበት ምክንያት ግን የአብዘርድን ፍልስፍና ወደፊት ለማራመድ ነው። በተውኔቱ ውስጥ ለምረዳት እንደ ምንችለው የህይወትን አሰልቺነት፣የመፈጠርህ አላማ ምንድን ነው፣በህይወታችን ውስጥ አዲስ ነገር የለም እነዚህን እና ለሎች የአብዘርድ ሃስቦችን ቃለተውኔቶቹ ተሸክመውት እንመለከታለን።

### 3.2.4 “የእንግዳ” ተውኔት ሴራ ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላል?

የአብዘርድ ሴራ ዘልማዳዊ ከሆነው የሴራ አገላለፅ የተለየ ነው። አጥኚው በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ እንደሞከረው የአብዘርድ ተውኔት በአንፃሩ አመክኗዊነትን የጠበቀ የተውኔታዊ መዋቅር መርህን ይቃረናል። አጠቀላይ ተውኔቱ በቅንጣት ትዕይንቶች እና በቁርጥራጭ ታሪኮች የተሞላ ሲሆን የእያንዳንዱ ቅንጣት ትዕይንት በምክንያት እና ውጤት የሚራመድ አይደለም። በዘልማዳዊ ተውኔት ውስጥ ስለገፀባህሪያት ስም፣ እድሜ፣ህይማኖት፣የትምህርት ሁኔታ፣እንዲሁም መቼቱ የት እንደሆነ እውቂያ የሚደረግ ሲሆን እነዚህን ሀሳቦች አጥኚው በገፀባሪያት ትንተና እና በመቼት ትንተና ውስጥ አካቷቸዋል።አብዘርድ ተውኔት በቅንጣት ትዕይንቶች እና በቁርጥራጭ ታሪኮች የተሞላ ነው። እያንዳንዱ ትዕይንት በምክንያት እና ውጤት የሚራመድ አይደለም። በእንግዳ ተውኔት ውስጥም በቁርጥራጭ ታሪኮች የተሞላ ነው ሲሆን እያንዳንዱ ቁርጥራጭ ታሪኮች በምክንያት እና በውጤት የሚራመዱ አይደለም።ለዚህ ማሳያ አጥኚው እንደሚከተለው ያቀርባል።

*“ባል - ዛሬ ቀፎኛል ጓደኞቼ ጋር ስሄድ አንዲት ሴትዮ ባዶ እንስራ ተሸክማ አቋረጠችኝ*
*ሚስት - የደናቁርት እምነት እያልክ ስታሾፍ አልነበረም*
*ባል - ያን እኮ ነው የምልሽ ከዚህ በፊት የማላምንበት ነገር ለምን በድንገት ዛሬ ረበሸኝ*
*ሚስት - ግን አንድ ሰው በክብረ ጋብዞ በመጣበት እግሩ መመለስ አሳፋሪ አይመስልህም*
*ባል - ግን ለምንድነው እቤት መቀመጥ የማትወጂው” (እንግዳ፤5)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ ሶስት የተለያዩ ቁርጥራጭ ታሪኮች አሉት። የመጀመሪያው ስለአጉል እምነቶች ሲያወራ ሁለተኛው ደግሞ ስለእንግዳው ያወራሉ። በነዚህ ሶስት ቁርጥራጭ ታሪኮች ውስጥ ምንም አይነት የምክንያት እና የውጤት ግንኙነት እንመለከታለን።

የአብዘርድ ተውኔት የሴራ መዋቅር የሌላቸው ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ክብ በሆነ የሴራ መዋቅር ውስጥ ይዋልላሉ። ይህ ማለት ሴራው ሳይጠናቀቅ የሚቋጭ ይሆናል። ይህን ሀሳብ በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ሰፍሮ የሚገኝ ነው።

በአብዘርድ ተውኔቶች ውስጥ ሴራዎች ሊፈቱ የማይችሉ እና የተወሳሰቡ ሚስጥሮች ናቸው። በእንግዳ ተውኔት ውስጥም ባል እና ሚስት የእውነት ይፋቀሩ አይፋቀሩ አንዳቸው ለአንዳቸው ለአንዳንቸው ይተሳሰቡ አይተሳሰቡ ይከባበሩ አይከባበሩ አይታወቅም ሚስጥራዊ ናቸው።

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ተደራሲው የተውኔቱ መጨረሻ ይህ ይሆናል ብሎ መገመት አይችልም። ምን እያደረጉ እና ምን እያወሩ እንዳሉ እንኳን መገመት አይቻልም። በእንግዳ ተውኔት ውስጥም የተውኔቱ መጨረሻ ይሄ ነው ብለው ተደራሲው ሊገምቱ አይችሉም። መጀመሪያውን ወይም መሀል ላይ አይተዉ እንግዳ ተውኔት እንዲህ ሁኖ ሊጠናቀቅ ይችላል ብለው ሊናገሩ አይችሉም። ምክንያቱም በእንግዳ ተውኔት ላይ ባል እና ሚስት በሚፈጥሩት ታሪክ እንግዳን ሲጫወቱበት እንመለከታለን። ይህ ግን ጨዋታ መሆኑን የምናውቀው በገፅ 26 ላይ "ሁለት ባል እና ሚስት ህይወት ሰልችቷቸው ቤታቸው ውስጥ በየቀኑ አዳዲስ እንግዳ እየጋበዙ በእግዳው ላይ ለመዝናናት ይሞክራሉ።" ከገፅ 26 በፊት የነበረው የባል እና የሚስት የፈጠራ ጨዋታዎች የውሸት እንደሆኑ አይታወቅም ነበር። ተመልካቹ የሚሰማው ባል እና ሚስት የፈጠሩት የውሸት ሳይሆን እውነተኛ ታሪክ ነበር የሚመስላቸው። ለእንግዳው የፈጠራ ታሪክ እንደሆነ በገፅ 26 ላይ ከነገሩት በኃላ እንኳን ሚስት እና ባል በድጋሚ እንግዳ ላይ ይጫወቱበታል። ሚስት ባልን እንደምትጠላው እና እንደማታፈቅረው ነግራው ከእንግዳ ጋር ለመሔድ ስትነሳ ባል ወደ ውስጥ ገብቶ እራሱን ያጠፋል። ተሪኩ እዚህ ጋር አበቃ ሚስት ከእንግዳ ጋር ልትሄድ ነው ብሎ ተደራሲው ሲያስብ ባል ከውስጥ ይወጣል። ተደራሲው ከዚህ በኃላ ምን ሊፈጠር ይችላል ብሎ ሲያስብ ሚስት ይህ ጨዋታ እንደሰለቻት እና መጫወት እንደማትፈልግ ለባሏ ትነግረዋለች። ባልም እራሳቸውን እንዲያጠፉ ጥይት አምጥቶ ወደራሱ ለመተኮስ ሲታገል እና ሚስት ተቀብላ ወደራሷ ትተኩሳለች። በዚህ ሂደት ውስጥ ተደራሲው ባል እና ሚስት ቀጥሎ ይህን ያደርጋሉ ብለው ሊያስቡ አይችሉም።

### 3.2.5 "የእንግዳ" ተውኔት ጭብጥ ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላል?

የአብዘርድ ጭብጥ ብቸኝነት፣የመነጠልን፣ተስፋቢስነትን፣የህይወትን እና የሞትን እርባናቢስነት ያሳያል። የእንግዳ ተውኔት ጭብጦች ተስፋቢስነት፣የህይወት ድግምግሞሽ፣የህይወት እና የሞት እርባናቢስነት ናቸው። እነዚህ ጭብጦች እጥኚው እንደሚከተለው በማስረጃ አስደግፎ አቅርቧል።

*"ሚስት - ሁለቱ ባልና ሚስት ናቸው፡፡ ኑሮ በጣም የሰለቻቸው፡፡*

*ባል - አንድ ቀን ጊዜውን ለማሳለፍ ምን ቢያረጉ እንደሚሻል ሲወያዩ አንድ ሃሳብ መጣላቸው፣*

*ሚስት - እውነተኛ ቲያትር መሥራት!" (እንግዳ፤26)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ ባል እና ሚስት ምን ያህል ህይወት እንደሰለቻቸው መመልከት ይቻላል። ህይወት ብትሰለቻቸው እውነተኛ ቲያትር ለመስራት ያስባሉ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት አሰልቺ ህይወታቸውን ለመርሳት ነው።

*"ባል - ግን ሁሌም አዲስ እንግዳ መሆን አለበት፣ አለበለዛ አሰልቺ ይሆናል፣*
*ሚስት - ልክ እንደ ህይወት" (እንግዳ፤27)*

ሁሌም አዳዲስ እንግዳ ነው መሆን ያለበት ካልሆነ አንድ አይነት ድግምግሞሽ የበዛበት ይሆን እና ልክ እንደ ህይወት አሰልቺ ይሆናል

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ፀሀፈ ተውኔቶቹ ለአለም ያላቸውን እውነተኛ ስሜት ወይም ሊያስተላልፉት የሚፈልጉትን መልዕክት በአቀንቃኝ ገፀባሪያቱ አማካኝነት ይገልፃሉ። የሰው ልጅ በምድር የመኖር አላማው ትርጉም የለውም ብለው ስለማያምኑ በሚሰሩትም በሚፅፉትም ተውኔት ውስጥ አጉልተው ያሳያሉ። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ አቀንቃኝ ገፀባህሪ ከሆኑት መካከል ባል ለምን ወደ ወደዚህች ምድር መጣንለምን ተፈጠርን? የተፈጠርንበት አላማ አለ። አላማውስ ምንድን ነው እያለ ይጠይቃል።

*"ባል - አንድ ሰው መቼም ያላንዳች ምክንያት ወደዚህ አይመጣም*
*እንግዳ - ተጋብዤኮነው የመጣሁት*
*ባል - ወደዚች ምድር?" (እንግዳ፤10)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ ወደዚህች ምድር ያላአንዳች ምክንያት አልመጣንምእና ለምን ተፈጠርን? ሲል ባል ይጠይቃል። የመፈጠራችን አላማ ምንድነው ብለን የምንጠይቅ ከሆነ ምላሽ የሚሰጠን ግለሰብ የለም። አንድ ግለሰብ ለምንድነው የተፈጠርከው ተብሎ ቢጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ አይኖርም አልያም አጥጋቢ ምላሽ አይሰጥም። ምክንያቱም የሰው ልጅ በራሱ አቅም ሊመለሰው የሚችል ጥያቄ አይደለም።የዚህን እና የሌሎችን ጥያቄዎች መልስ ሲያጣ የሰው ልጅ በምድር ላይ የመኖር አላማው ትርጉም ያጣበታል።

የአብዘርድን ተውኔት ለመጀመሪያ ጊዜ ያነበበ ሰው በገፀባህሪያቱ እና በንግግራቸው ሊስቅ ይችላል። ነገር ግን በጊዜ ሂደት ወደ ጭብጡ እና ወደ እውነታው እንዲያይ ተውኔቱ እራሱ ያስገድደዋል። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ገፀባሪዎቹ እራሳቸው ምን ያህል ኑሮ እንደሰለቻቸው ማሳየት ብቻ ሳይሆን ባል እና ሚስት እራሱ ማህበረሰቡን ምን ያህል እንደሚበድሉት መመልከት ይቻላል። ይህቺ አለም ሁሉም እራስ ወዳድ ክፉ እና ጨካኝ የሆነባት አለም ናት። ባል እና ሚስት እዚህ አሰልቺ የህይወት ኑሮ ውስጥ እንዲገቡ የራሳቸው ምክንያት ቢኖራቸው ከዚህ ህይወት ለመውጣት ብለው በሌሎች ሰዎች ላይ ይጫወታሉ ። በአብዘርዳዊ ህይወት ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ወደዚህ ህይወት ከመግባታቸው በተጨማሪ ሌሎችን በዙሪያቸው ያሉትን ሰዎች ወደዚህ አብዘርዳዊ ህይወት ሊያስገቡ ይችላሉ። በጨዋታው ውሰጥ ሰለባ የሚሆነው ሰው በዚህ ጨዋታ እና በሌሎች ምክንያቶች ወደ አብዘርዳዊ ህይወት ሊገባ ይችላል። ለምን እኔ ላይ ይህን ጨዋታ መጫወት ፈለጉ? ለምንድነው የሰው ልጅ እርስ በርሱ እንደዚህ የሚጨካከነው? ለምድነው የሰውልጅ እራስ ወዳድ የሆነው? ለምንስ ተፈጠርን የሚሉ ጥያቄዎችን ሲጠይቅ ምላሽ ሲያጣ ድብርት ውስጥ ይገባእና አብዘርዳዊ ህይወት ይፈጠርበታል።

*"ሚስት - ከዛሬ ጀምሮ ይህ ጨዎታ ይቅር*
*ባል - ከዛስ?*
*ሚስት - ከዛማ ... እኔንጃ /ፋታ/ ሌሎች ባልና ሚስቶች ብቻቸውን ሲሆኑ ምን ይሆን*
*የሚሰሩት?" (እንግዳ፤35)*

አብዘርዲስቶች ሊያስተላልፉት የሚፈልጉት መልዕክት በግለሰቦች የሚነሱት ጥያቄዎች በሰው ልጆች አቅም ሊመለሱ የማይችሉ ናቸው ብለው ያምናሉ። አብዘርዲስቶች ከሚያነሡት ጥያቄዎች መካከል እኔ ማን ነኝ? ሰው መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ለምንድነው የምንኖረው? ደስታ እና መረጋጋትስ ምንድን ናቸው የሚሉትን ነው። የሰው ልጅ እነዚህን ጥያቄዎች ጠይቆ መልስ ማግኘት እንደማይችሉ ሲገባቸው ህይወት ይሰላቻቸዋል። ህይወት ሲሰለቻቸው ደግሞ ድብርት ውስጥ ይገባሉ። ከዚህ አስልቺ ህይወት እና ድብረት ለመውጣት የተለያዩ የመፍትሔ ሀሳቦችን ይወስዳሉ። በእንግዳ ተውኔት ዉስጥም ባል እና ሚስትም የተለያዩ የመፍትሔ ሀሳቦችን ይወስዳሉ በእንግዳ ተውኔት ላይም ባል እና ሚስት የተለያዩ የመፍትሔ ሀሳቦችን ተጠቅመው ነበር። ነገር ግን እነሱ በፈለጉት መጠን ከዚህ አስልቺ ህይወታቸው ሊያወጣቸው አልቻለም። ሚስት ከላይ በተገለፀው ቃለ ተውኔት ውስጥ ይህ እንግዳን እየጋበዙ የሚጫዎቱት ጨዋታ እነሱ ከሚፈልጉት አላማ ጋር አልገጠመም። ስለዚህ የህይወትን ትርጉም የለሽነት አምነው ልክ እንደሎች

ባለትዳሮች በትዳራቸው ደስተኛ ለመሆን ይሞክራሉ። አብዘርዲስቶች ከሚሰጡት የመፍትሔ ሀሳቦች መካከል የህይወትን አብዘርድነት አምኖ መቀበል ነው።

አብዘርዲስቶች ከእምነት ጋር የተያያዙ ማንኛውም ነገሮችን ይቃወማሉ ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ የየትኛውም እምነት ፈጣሪ የሆነው በህይወታችን ውስጥ ለሚፈጠረው እያንዳንዱ ነገር እና ለምንጠይቀው ሁሉ ምላሽ ሊሰጠን አልያም መፍትሄ ሊኖረው ይገባል ብለው ያምናሉ። አብዘርዲስቶች ማህበረሰቡ ተስማምቶ የሚያከናውናቸውን ክዋኔዎችን ምክንያቱን የማያውቁት ከሆነ ድርጊቶችን ይቃወማሉ። ለምንድን ነው የምናደርገው?ድርጊቱ ደስታንስ ይሰጣል?ድርጊቱን ስንከውን የምናገኘው ምንድን ነው?ድርጊቱን ባንከውነውስ የምናጣው ነገር አለ ወይ?ማነውስ እነዚህን ልማዶች የሰጠን? እነዚህን እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ይጠይቃሉ። ለጥያቄያቸው ምላሽ ሲያጡ እነዚህን ማህበረሰቡ ተስማምቶ የሚከውናቸውን ድርጊቶች አብዘርዲስቶች በመተው እራሳቸውን ከማህበረሰቡ ይገነጥላሉ። ማህበረሰቡም ከዚህ ቀደም ያምንበት የነበረን ነገር ስህተት ናቹህ ሲባሉ ተናጋሪውን አካል ከማህብረሰቡ ያገሉታል። ይህ ከማህብረሰቡ ያፈነገጠ ግለሰብ ማህበረሰቡን በመቃወሙ የብቸኝነትን ህይወት እንዲገፋ ይገደዳል። ይህ የብቸኝነት ህይወት ደግሞ ወደ አብዘርዳዊ የድብርት እና አሰልቺ ህይወት ይገፋዋል። በእንግዳ ተውኔት ውስጥም ባል አጉል ልምዶችን ይቃወም እንደነበር አጥኚው እንደሚከተለው ተመልክቷል።

*"ባል - .............ቅድም ጓደኞች ጋር ስሄድ አንዲት ሴትዮ ባዶ እንስራ ተሸክማ አቋረጠችኝ።*

*ሊጋጣሚ ይሆናል ብዬ ትንሽ እንደሄድኩኝ ከዛው አቅጣጫ አንዲት ነጭ ድመት*

*በግረ ላይ ሮጣ ሄደች....*

*ሚስት - ........የደናቁርት እምነት ኢያልክ ስታሾፍ አልነበር?" (እንግዳ፤7)*

## 3.3 እንግዳ ተውኔት ከአብዘርድ ተውኔት መለያ ባህሪያት አንጻር

### 1. የመኖር ጥያቄ

የአብዘርድ ተውኔቶች መሠረታዊ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ። ለምድነው በህይወት የምንኖረው? ለምንድንስ ነው የምንሞተው? ለምንስ ግፍ እና ስቃይ ይደርስብናል።

*"ባል - አንድ ሰው መቼም ያላንዳች ምክንያት ወደዚህ አይመጣም*

*እንግዳ - ተጋብዤኮነው የመጣሁት*

*ባል - ወደዚች ምድር?" (እንግዳ፤10)*

በዚህ ቃለተውኔት ውስጥ ባል የመኖር ጥያቄ እንግዳን ይጠይቀዋል።ለምንድን ነው ወደዚህች አለም የመጣነው፣ለምንድንስ ነው የተፈጠርነው፣የሚሉትን ጥያቄዎች ይጠይቃል። ሌላኛው ሚስት በእናቷ ምን ያህል ግፍ እና ስቃይ ይድርስባት እንደነበር ለእንግዳው ትተርክለት ነበር በገጽ 22 ላይ።

## 2. ትርጉም አልባ ቃለ ተውኔት

በአብዘርድ ተውኔት ውስጥ ቋንቋ ትርጉም አልባ ነው። ምክንያቱም ቋንቋቸው የሰውን ልጅ የመኖር ህልውናዊነት ስለማይገልፅ።

በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ቃለተውኔቶቹ አብዘኛውን ጊዜ ትርጉም የሚሰጡ፣ገጸባህሪዎቹ የሚግባቡበት ነው። ነገር ግን ቃለትውኔቶቹ የአብዘርድን ጽንሰ ሃሳብ የተሸከሙ ናቸው። ለዚህ ማስረጃው ደግሞ አጥኚው 3.2.3 “የእንግዳ” ተውኔት ቃለተውኔት ከአብዘርድ የተውኔት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላል? በሚለው ርእስ ስር ለመተነተን ሞክሯል።

## 3. የሰው ልጅ ከዓለም ጋር በድጋሚ እንዲስማማ ማድረግ

ተረት እና የአለም ስርአቶችን በሰው ልጅ ህይወት ወስጥ ያለውን ጠቀሜታ መመለስ እና የህይወትን የመጨረሻ እውነታዎች እንዲረዱ ማድረግ።

አብዘርዲስቶች ከሚጠቀሙአቸው የመፍትሄ ሃሳቦች መካከል አንደኛው የሰው ልጅ ከአለም ጋር በድጋሚ እንዲግባባ ማድረግ ነው። በአለም ላይ ምንም አዲስ ነገር የለም ከሚለው እስቤያቸው እንዲወጡ አንደኛው መፍትሄ በፊት ይጠቀሙቸው የነበረውን ስራአት ለምሳሌ እንደ ባህል፣ሃይማኖት፣ወግ፣ልማድ እና የመሳሰሉትን መመለስ ነው። በእንግዳ ተውኔትም ላይ ባል በፊት የማያምንበት የነበረው አሁን ላይ ግን ለማመን ልቡ ሲያምነታ ይስተዋላል። ለዚህ ማሳያ ደግሞ በገጽ 5 ላይ ሚስት “ከዚህ በፊት የደናቁርት እምነት እያልክ ታሾፍ አልነበር ብላ ስጠይቀው ባልም ያን እኮ ነው የምልሽ ከዚህ በፊት የማላምንበት ጉዳይ ለምን ዛሬ ላይ ይረብሸኛል” ይላታል።

## 4. ረቂቅ የህይወት እሴቶች ላይ አፅንኦት መስጠት

የአብዘርድ ተውኔቶች ግፊት ያደርጋሉ እንደ ፍቅርና እና ቤተሰብ ያሉ ረቂቅ ጉዳዮችን እንድንመለከት ያስገድደናል። ስለዚህ የህይወትን ትርጉም የለሽነት አምነን እንድንኖር ያደርጋል።

የአብዘርድ ትውኔቶች የአለምን ትርጉም አልባነት፣የአለምን ጨለማነት የሚያሳዩ ሲሆን በዚህ ሂደት ውስጥ ግን ብርሃንን ሲፈልጉ ይስተዋላል። በአብዘርዳዊ ሂይወት ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ከሚውስዷቸው የምፍትሄ ሃስቦች መካከል አንደኛው የሂይወትን አብዘርድነት አምነንን መቀበል ነው። የሂይወትን አብዘርደነት አምነን

ስንቀበል ደግሞ በድጋሚ ወደዚህ አብዘርዳዊ ህይወት እንዳንመለስ ፍቅር እና ቤተሰብ አንደኛው መፍትሄ ነው። በእንግዳ ተውኔት ውስጥም በድጋሚ በተሰብ ለመሆን ይስማማሉ። ልክ እንደሌሎቹ ባል እና ሚስቶች ተስማምተው መኖር እንዳለባቸው ሚስት ሃሳብ ታመነጫለች። በገጽ 35 ላይ

ሚስት- ከዛማ ... እኔንጃ /ፋታ/ ሌሎች ባልና ሚስቶች ብቻቸውን ሲሆኑ ምን ይሆን የሚሰሩት?

## 5. በገፀባሪዎች መካከል የግንኙነት አለመኖር

እያንዳንዱ ገፀባህርይ የራሱን ግላዊ ኑሮው የሚኖር ሲሆን እሱን እንዲረዳው ሌላ ገፀባህርይ ለማግኘት ይሞክራል እናም ይህ ሙከራ የበለጠ በሁለቱ በገፀባህሪዎች መካከል እርቀትን ይፈጥራል። በእንግዳ ተውኔት ላይ ባል እና ሚስት የራሳቸውን ግላዊ ሂይወት የሚኖሩ ሲሆን በቤታቸው ውስጥ እንግዳ ይጋብዛሉ። እንግዳ የሚጋብዙበት ምክንያት አሰልቺ ህይወታቸውን ለመርሳት ሲሆን በእንግዳ እና ባል እና ሚስት መካከል ከፍተኛ እርቀት ነበረ። ይህ እርቀት ደግሞ ከፍተኛ ጸብን አስነስቷል።

# ምዕራፍ አራት

## 4. ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ

### 4.1. ማጠቃለያ

አጥኚው በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ እንግዳ ተውኔትን ከአብዘርድ ቴአትር መለያ ባህሪያት አንጻር ትንታኔ ሰጥቷል። አብዘርድ ተውኔት የሰውን ልጅ ህይወት አብዘርዳዊነት ለማሳየት ኢ ተአማኒ እና ትርጉም የለሽ ግራ በሚያጋቡ ድርጊቶች እና ቃለ ተውኔቶች የሚጠቀም የተውኔት አይነት ነው። አንድ የአብዘርድ ቴአትር ጸሃፊ በመድረክ ላይ ለሚያሳየው ተውኔት የአብዘርድን መለያ ባህሪያት በሚገባ ተጠቅሞ ሊጽፍ ይገባል። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ የሂወትን አሰልቺነት፣የእርስ በርስ ጭካኔ፣የእንግዳ አያያዝ፣የልማድን አስከፊነት እና የመሳሰሉትን አጥኚው ተመልክቷል።

እንግዳ ተውኔት በውስጡ የታሪክ አወቃቀሩ እና ፍሰቱ፣የጭብጡ አስፈላጊነት፣የሴራ አወቃቀሩ፣ የመቼት አጠቃቀሙ የገጸባህሪያት አሳሳሉ ከአብዘርድ ቴአትር መለያ ባህሪያት እና ከአብዘርድ የተውኔት አላባውያን አንጻር አጥኚው ተንትኗል። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ገፀባህሪያቱ ትርጉመ ቢስ፣ቃለተውኔቱ የአብዘርድን ጥያቄዎች ተሸክሞ የያዘ፣መቼቱ የጊዜ እና የቦታ አንድነት ያለው (አንድ ቤት ውስጥ ተጀምሮ የሚያልቅ ነው) ስራዎቹ በምክንያት እና ውጤት የተደገፈ አይደለም። የእንግዳ ተውኔት ጭብጥ የአብዘርድን አላማ የሚያሟላ ነው።

አጥኚው በእንግዳ ተውኔት ላይ ያስተዋለው ችግር የገጸባህሪያቱ አሳሳል የአብዘርድን ጽንሰሃሳብ ሙሉ ለሙሉ የሚያሟሉ አይደሉም። ለዚህ ማስረጃው ደግሞ በምእራፍ ሶስት ላይ ገጸባህሪያቱን አጥኚው ሲመለከተው በግማሽ ዘልማዳዊ የገጸባህሪያት አሳሳለን የተከተሉ ናቸው። ለምሳሌ ባል፣ሚስት እና እንግዳን ስንመለከታቸው ስለቤተሰባቸው፣ስለሙያቸው፣ስላለፈ የሂይወት ታሪካቸው በከፊልም ቢሆን ተገልጸው እናገኛቸዋለን። ይህ ደግሞ ከአብዘርድ የገጸባህሪያት አሳሳል አንጻር ስንመለከተው የሚጋጭ ነው። በእንግዳ ተውኔት ላይ ቃለተውኔቶቹ አጥኚው ሲመለከተው የአብዘርድን ጽንሰ ሃሳብ የብዘርድን ጭብጥ የሚሸከም ቢሆንም የአብዘርድን ኢ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የቀረበ አይደለም። ይህ ደግሞ የአብዘርድን ጽንሰ ሃሳብ የሚጣረስ ነው። ምክንያቱም በአብዘርድ ቋንቋ ውስጥ ገጸባህሪዎቹ የሚናገሩት እርስ በርስ የሚቃረን ነው። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ግን ቃለተውኔቶቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም። ገጸባህሪዎቹ እርስ

በርሳቸው የሚግባቡ ናቸው። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ የመቼትን አገላለጽ ከአብዘርድ አገላለጽ አጥኚው ሲመለከተው ቦታው የሚታወቅ ቢሆንም ቦታው ኻ የማይቀየር አንድ ቦታ ላይ ነው።

በአጠቃላይ በእንግዳ ተውኔት ውስጥ የአብዘርድ የተውኔት አጻጻፍ ስልት በከፊል የተተገበረበት ሲሆን ወደፊት በአብዘርድ የተውኔት አጻጻፍ ላይ ተመርኩዘው ለሚጻፉ ትምህርት የሚሆን ጥሩ የሆነ ጽሁፍ ነው።

## 4.2. **የመፍትሔ ሀሳብ**

አጥኚው ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ እንግዳ ተውኔትን ከአብዘርድ የተውኔት መለያ ባህሪያት እና ከአብዘርድ የተውኔት አጻጻፍ አንጻር ለመተንተን ችሏል። ከነዚህ እሳቤውች አንጻር አጥኚው ሊቀረፉ ይገባሉ ብሎ የሚያምናቸውን እንደሚከተለው አስቀምጧል።

በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ቃለ ተውኔቶች የአብዘርድን ጽንስ ሃሳብ የተሸከሙ ቢሆንም ከዚህ በላይ የአብዘርድን ፍልስፍና ደራሲው መግለጽ ይችል ነበር። እንግዳ ተውኔት የአብዘርድን ጽንጸ ሃሳብ ከዚህም በላይ  በጥልቀት መግለጽ ይችል ነበር። የሂወትን አሰልቺነት ደራሲው በተለያዩ መንገዶች እና በተለያዩ ሃስቦች መግለጽ ይችል ነበር። በእንግዳ ተውኔት ውስጥ ገጸባህሪያት፣መቼት፣ቃለተውኔት እነዚህ ሁሉ ሙሉ ለሙሉ የአብዘርድን የተውኔት አጻጻፍ የሚያሟሉ አይደሉም። የብዘርድን የተውኔት መለያ ባህሪያትን እና የአብዘርድን የተውኔት አላባውያን አጻጻፍ በሚገባ ደራሲው ቢጠቀማቸው ከዚህ በተሻለ ህሳቡን መግለጥስ ይቻል ነበር።

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. 'Absurd' originally means 'out of harmony', in a musical context. Hence its dictionary defnition: 'out of harmony with reason or propriety; incongruous, unreasonable, illogical'. In common usage, 'absurd' may simply mean 'ridiculous',
2. absurd is that it is "the divorce between man and his life, the actor and his setting
3. The absurd is born of this confrontation between the human need and the unreasonable silence of the world
4. 'Absurd is that which is devoid of purpose. ... Cut of from his religious, metaphysical, and transcendental roots, man is lost; all his actions become senseless, absurd, useless.'
5. Absurdism as a philosophy refers to the fundamental nature of conflict in human tendency to find meaning and inherent value in life and inability in the same in a purposeless existence in an irrational universe
6. Even though Theatre of the Absurd plays were being written by playwrights well known in 1939 and the plays became popular by the early 1950s
7. Theatre of the Absurd or absurdism is a movement where theatre was less concerned with a plot that had a clear beginning, middle, and end, but dealt with the human condition. Two major playwrights of this time were Samuel Beckett and Eugene Ionesco. Samuel Beckett's plays tended to deal with the human condition in the metaphysical sense while Eugene Ionesco's plays tended to deal with social relationships
8. **Questions of Existence**
   Absurd plays raise some basic questions of existence like- why we are alive why we have to die and why there is injustice and sufering.
9. **Distrust in Language**
   For absurdist playwrights, language is only a meaningless communication and stereotyped exchange of ideas because words fail to express essence of human existence.
10. **Illogical Speeches and Meaningless Plots**
    By illogical speeches and meaningless plots, they wish to establish a feeling of freedom to make their own worlds. Dr. Culik says,
11. **Re-establishment of man's communion with Universe**
    They attempt to restore the importance of myth and rituals in the life of man and make them aware of the ultimate realities of their life.
12. **Emphasize on Abstract Values of Life**
    Absurdists force us to look at our abstract values of life like love and family. Thus, we may hope to accept the absurdity of life and try to and values in a world devoid of them.

13. **Vagueness about Time, Place and Character**
Absurdists have no time, place and character in their plays as they feel that there is no past or future,only the repetition of the present
14. **Lack of communication amid characters**
Each character lives an egoistic life and attempts to get another character to understand him and this results in more alienation.
15. the main character in a play we automatically accept his point of view see the world in which he moves with his eyes
16.The more complex characters are in crisis because the world around them is Incomprehensible
17. The element of language still plays an important part in this conception, but what *happens* on the stage transcends, and often contradicts, the *words* spoken by the characters
18. Despite its reputation for nonsense language, much of the dialogue in Absurdist plays is naturalistic.
19. Absence, emptiness, nothingness, and unresolved mysteries are central features in many Absurdist plots
20. The plots of many Absurdist plays feature characters in interdependent pairs, commonly either two males or a male and a female.
**21.** Asimilar sense of the senselessness of life, of the inevitable devaluation of ideals,purity, and purpose, is also the theme of much of the work of dramatists of absurdist

# ዋቢ መፅሀፍት


ማንያዘዋል እንዳሻው።እንግዳ።

የሻው ተሰማ።(1998) ዓ.ም።የተውኔት አፃፃፍ መነፀር።አዲስ አበባ።

ያለው እንዳወቅ ሙሉ።(2009)።የምርምር መሠረታዊ መርሆዎች አተገባበር።ባህርዳር ዩኒቨርስቲ።ሊትማን መፅሀፍት።

ደበበ ሰይፉ።(1973) ዓ.ም።የቲያትር ጥበብ ከፀሀፊ ተውኔቱ አንፃር።አዲስ አበባ።በንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ።

ፋንታሁን እንግዳ።(1993) ዓ.ም።ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ሀ እስከ ፐ።አዲስ አበባ። ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

______።የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ። (2009) ዓ.ም።አዲስ አበባ።አርቲስቲክ ማታሚያ ድርጅት።

ጫንያለው ወ/ጊዮርጊስ፣ተስፋዬ ገ/ማርያም፣አስታጥቃቸው ይሁን፣እቴነሽ ካሳ፣ዓለማየሁ ታደሰ።(2009)። መሠረታዊ የተውኔት አፃፃፍ መርሖዎች።አዲስ አበባ።በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ።

Alan Astro. *Understanding Samuel Beckett*. Univ of South Carolina Press, (1990,116)

Allan Lewis, (1966),"TheTheatre of the 'Absurd' – Beckett, Ionesco, Genet". The *Contemporary Theatre: The Significant Playwrights of Our Time*, Crown Publishers,

Brockett, Oscar G., and Franklin J. Hildy, (2008), *History of the Theatre*, Reprint. Boston: [Allyn and Bacon]

JARED L. SMITH, (2020), FROM ONE TO ALL: THE EVOLUTION OF CAMUS'S ABSURDISM, Kent State University,

Martin Esslin, (1961), The Theatre of The Absurd, Usa, Anchor Books Edition

## ድህረ ገጾች


**Ansel Pereira, (2019)**, *humanities the-philosophy-of-absurdism, owlcation*

Somnath Sarkar, (may 28,2021),***theatre-of-the-absurd-definition-examples-characteristics***